# ያነቡ እንባዎች

በዛብህ ብርሀኑ



Scanned with CamScanner



በፍጥረት መንገድ ፣ ላይ የሚማስነው፤
በአይኑ ከረጢት ፣ አዝሎ የሚዞረው፤
ሁሉም ዘረ አዳም፤
የራሱ እንባ አለው።

ዋጋ ፡ 101 ብር

Scanned with CamScanner

# ያነቡ እንባዎች

## (ስብስብ ስራዎች)

በበዛብህ ብርሃኑ (Base)

2013 ዓ.ም

Scanned with CamScanner

© መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

2013 ዓ.ም ታተመ

ለአስተያየት : base.birhanu@gmail.com

(0927154173)

ግራፊክስ ዲዛይን : ቴዎድሮስ መኮንን

(0919668741 Hope graphics)

አርታኦት :- ዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አእምሮ

## መግቢያ

በዛብህ ታታሪ ወጣት ነው። የሐዋሳ ሐይቅ ተራጭቶ እንደማደጉ አሁንም ከአሞራ ገደል የመዘዘውን ላብ በሐይቅ ቀለም ውስጥ እየነከረ ይጽፋል፣ ይገጥማል፣ ፊልም ይጽፋል፣ ኹነቶች ያቀናጃል። እሱን፡ የዚህ መልከ ብዙ ትውልድ አንዱ ፍላጻ አድርጎ መመሰል ይቻላል።

ይህቺን አዲስ ድርሳኑን ገልጬ "ያነቡ እንባዎች" የሚለውን ርዕስ ሳነብ፣ ከዚያም በስሱ ስዘልቅ የተመላለሰብኝ ያልተነቡ እንባዎች ማዕበል ነበር። ጥቂቶች ብቻ ናቸው ማልቀስን የታደሉ ፤ በወጎቹና ግጥሞቹ ውስጥ ያሉ ትዝታና ምልከታዎቹ ብዙ ጊዜ ፈንቅለውን ያልወጡ ቅጽበቶች ሲለጥጥ እናገኛዋለን። ሐዘንና ደስታ፣ ፍቅርና ናፍቆት፣ እንባና ሳቅ... ሳቅ እራሱ እንባ ሲሆን ትታዘባላችሁ

Scanned with CamScanner

በዜ ይህቺን ሁለተኛ ልጅህን እንኳንም በሰላም ለመገላገል አበቃህ። ገና ብዙ ካንተ እጠብቃለሁ።

(ዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አእምሮ)

"ያነቡ እንባዎች!" ባልተለመደ አቀራረብ፤ በለስላሳና ሸንቋጭ ቃላት ተሰናትረው እያዝናኑ በግጥም አስጀምረው ስሜቱን ለማጣጣም ስንሞክር ወደ ወግ ወንዝ ያስገቡናል። በ..ጀ ብለን ስንወጣ እንደገና ግልፅ እና ጣፋጭ ግጥሞች ከራሳቻው ጋር ያጣብቁናል። ..እንዲህ እያልኩ ለማንበብ የማያታክቱትን ይልቁኑ ሲይዟቸው እልም ጭልጥ የሚያደርጉትን በርካታ ቁምነገሮች ዘና እያደረጉኝ አንብቤያቸዋለው። እናንተም የወጣት በዛብህ ብርሃኑን ስራ ተቋደሱ፣ ተዝናኑ፣ ተፈላሰፉ፣ እንዳሻችሁ! ግን የማዕዱን አቅራቢ ወጣት በዛብህን አበረታቱ አመስግኑ።እኔ እደግልን ብያለው።

( ስመጥሩ ታዬ ደራሲ እና የላይፍ መጽሔት ዳይሬክተር)

Scanned with CamScanner

እንባ ለኛ ለሰው ልጆች በተለይም ለኛ ለኢትዮጵያውያን ከፈሳሽ ዘለላ ባለፈ ብዙ ትርጉም አለው። ለህመም ማስታገሻ ፤ ለትዝታ መተከዣ ፣ ለሚች አፈር ማቅለያ ፣ የደስታችን ጡዘት ማዳረሻ ነው። ስለእንባ ማህበረሰባችን ብዙ ብሏል።

በአሉ ግርማ "እንባ እንባ ይለኛል ይተናነቀኛል" ሲል የመተናነቅን ስሜት እንባ እንደሚተካው በስንኙ ቋጥሮ ሲያስረዳን ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ደግሞ "ወንድ ብቻውን ነው ሚያለቅስ" በሚለው ግጥሙ እንባ እንዴት ወንድነትን እንደሚፈታተን በፈርጣማ ውብ ቃላቶቹ ያወጋናል። ዛሬ ደግሞ ግዜ ቆጥሮ በዛብህ "ያነቡ እንባዎች" በተሰኘው ሁለተኛ መፅሀፉ የሚያነቡ እንባዎችን በአጫጭር ታሪኮች ያወጋናል። በግጥሞቹ ያዋዛናል ፣ በገፀ-ባህሪዎቹ ያጫውተናል ፣ በታሪኮቹ ወደ እንባው መንደር ይወስደናል።

(በረከት ይሄይስ የቴአትር ጥበባት መምህር)

## የደራሲው መልዕክት

መፅሃፍ ፅፎ ማሳተም ማለት ልጅ ወልዶ ስሞ ከዚያም አልፎ ለወግ ማዕረግ ማብቃት ወይም መዳር ነውና በአንዲዬ ቸርነት እኔም የይሁዳ ገመድ ታናሽ እህት የሆነችውን ያነቡ እንባዎች የተሰኘችውን ሁለተኛ ልጄን ለወግ ማዕረግ ለማብቃት በቃው።

ይህች ሁለተኛ ልጄ በአስተዳደግም በልቧ ፅላት ላይ ለማተም በሞከርኩት የህይወቷ ፋና የራሷን መልክ እና ቀለም ይዛ የመጣች መሆኑን እና አንድ አባት ስለ ልጁ በድፍረት እንደሚያወራው ሁሉ እኔ ስለ ልጄ ይህን ብያለው።

ቸር ቆይታ ይሁንላችሁ !!

Scanned with CamScanner

## ምስጋና

- ከሁሉም በላይ ለረዳኝ ለቸሩ መድሃኒያለም ምስጋና ይደረስልኝ!
- ፅሁፎችን በመገምገም መልካም የሆነውን አስተያየት ለሰጣቹኝ ጓደኞቼ ቤተሰቦቼ እና ሙያዊ የሆነ ሀሳብ ለለገሳቹኝ ወዳጆቼ ለዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አእምሮ ፡ የቴአትር ጥበባት መምህር ለበረከት ይሄይስ እንድሁም ደራሲ እና የላይፍ መጽሔት ዳይሬክተር ለስመጥሩ ታዬ ለእናንተም ምስጋናየ ከፊ ያለ ነው።
- ይህ መፅሃፊ እንዲፃፊ እና ለህትመት እንዲበቃ በሁሉም አቅጣጫ ለረዱኝ ለአቶ አርጋው አየለ ፡ እንዲሁም ለታላቅ ወንድሜ ለጋዘጤኛ ሙሉቀን ብርሃኑ ምስጋናዬ ወሰን የለውም
- በተጨማሪም ለሀዋሳ ሳውዝ ስታር ሆቴል
- ለፋሚሊ ማስታወቂያ እና ህትመት ስራ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ።

Scanned with CamScanner

## ማውጫ

አርእስት ገፅ

ያነቡ እንባዎች አንድ .................................... 12
ያነቡ እንባዎች ሁለት.................................... 13
ያነቡ እንባዎች ሶስት .................................... 16
ያነቡ እንባዎች አራት .................................... 19
ያነቡ እንባዎች አምስት.................................... 25
ያነቡ እንባዎች ስድስት .................................... 29
ያነቡ እንባዎች ሰባት .................................... 31
ያነቡ እንባዎች ስምንት.................................... 32
ያነቡ እንባዎች ዘጠኝ .................................... 65
ያነቡ እንባዎች አስር .................................... 79
ያነቡ እንባዎች አስራ አንድ ........................... 81
ያነቡ እንባዎች አስራ ሁለት ........................... 82
ያነቡ እንባዎች አስራ ሶስት ........................... 91
ያነቡ እንባዎች አስራ አራት ........................... 92
ያነቡ እንባዎች አስራ አምስት ........................... 95
ያነቡ እንባዎች አስራ ስድስት ........................... 100
ያነቡ እንባዎች አስራ ሰባት ........................... 102
ያነቡ እንባዎች አስራ ስምንት ........................... 103

Scanned with CamScanner

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)

Telegram Channel

## ያነቡ እንባዎች አንድ

በፍጥረት መንገድ ፡ ላይ የሚማስነው፤

በአይኑ ከረጢት ፡ አዝሎ የሚዘረው፤

ሁሉም ዘረ አዳም፤

የራሱ እንባ አለው።





## ያነቡ እንባዎች ሁለት

በሰማይ ገፅ ላይ የሚታይ አንዳች ነገር የለም። የፀሃይ ሳቅ ፡ የጨረቃ ፈገግታ ፡የኳክብቶች ፍንደቃ ፡ከወትሮው ይልቅ ዝም !ፀጥ ረጭ ጭጭ ብሏል ፤ እግዜርም በዝምታ ዘረ አዳምን መመልከቱን ቀጥሏል።

የአዳም ዘር ሁሉ በጭንቀት ተውጧል ፤ ፍርሃት ከበታል ዘር ብሄር የተማረ ያልተማረ ህፃን አዋቂ ሊህቅ ደቂቅ

የማይል የጋራ ወዳጅ ያጣውን የአለምን ህዝብ ሰብስቦ አንድ ሊያደርግ አንድ የጋራ ጠላት የእግዜርን አምሳሎች የፍርሃት ማቅ አለበሰ ። በኢኮኖሚ ፈርጣማ ነን የሚሉትን ሀገሮች ጉልበታቸውን ፈተነ፤ የአዳም ዘር እና ሞት የፊጥኝ ተፋጠጡ ፡ ዘረ አዳም ቋንቋው አንድ ሆነ። ስለ እሱ ለፈፈ ፤ ስለ እሱ አወጋ ፤ ውግዝ ሰባሪዎስ ሀጢይ ወንጀለኛ ብሎ ሊያጠፋው ዘመተ። እግዜርም ሴይጣንም ዝም አሉ ዝምታን መረጡ ።

*የሰው ልጅ ብቻውን እንደ ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ጮኸ።* ጥርሶች ተከደኑ ፡ አይኖች እንባ አረገዙ እልፍ ታማሚዎች በሆስፒታል ሞሉ ፤ አለም ግራ ገባት በጭንቅ ተዋጠች፤ እግዚዮ በሰማይ !እግዚዮ በምድር! እያሉ የሰማይን ደጆች አስተጋቡ። እርሱ ምንም አላለም አሁንም ዝም! ብዙዎች በራቸውን ደጃቸውን ዘግተው ለመቀመጥ ተገደዱ፡ በፍርድ ፊት የተቀመጠው ዘረ አዳም ጠላቱን ማጥፋት አቃተው ፡ ደከመ ፤ ከሰመ፤ ከሰለ ፤ ጉልበቱ ማቀቀ፤ ከሞት ጋር አብዝቶ ታገለ ግን አልቻለም ፡





ያደላቸውን ደረት እየተደቃ ሙሾ እየተደረደረ በወዳጆቻቸው እንባ እየተሸለሙ በሀገሬቱ ወግ እና ባህል ሥርዐት መሰረት ከምድር አፈር በታች ሆኑ።

ገሚሶቹ የሞት ሞት ሞቱ ፤ እንደ ዘር በየሜዳው ተዘሩ የእናቶች እንባ ከፋ ለሰርግ የታሰቡ ድንኳኖች ለለቅሶ ሆኑ ፤ በዝናብ ፈንታ የሞት መልአክቶች ዘነቡ ፡ ጥረህ ግረህ በላብህ ሰርተህ ብላ ያለው የፈጣሪ ቃል እሩቅ መሄድ አቃተው ።

የስራ ቦታዎች ተዘጉ የእምነት አባቶች ወደ ቤታቸው ተመለሱ ቤተ- እምነቶች በጋን ተከረቸሙ። ኑሮው ለየቅል ሆነ አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት ሰርክ ራቀ ተማሪዎች ወደየ ቤታቸው ተሰደዱ የጠቆሩ ፊቶች የቀሉ አይኖች ደጋግመው አለቀሱ፤ እንባዎችን አነቡ። ተስፋ የማይቆርጠው ዘረ አዳም አሁንም መሀረቡን ፍለጋ ይዳክራል።



Scanned with CamScanner

## ያነቡ እንባዎች ሶስት

. . . . ያንን ሁሉ ጊዜ ከእርሱ ጋር ኖረዋል ፡ ሸቅቡን ሲወጡ ዝናብ እና ፀሃይ እየተፈራረቀባቸው ወገባቸው ተፈትኖ ጉልበታቸው ዝሎ አይሆኑ ሆነዋል ። መራብ ፡ መጠማት ለእነሱ አዲስ ነገር አይደለም ። ከልክ በላይ መብላት መጥገብ ቤታቸውን በእህል መሙላት ለአስራ ሁለቱም እንግዳ ነገር አይደለም ። አዎን በእርግጥም ተርበዋል ፡ ተጠምተዋል ምግብን ፍለጋ በብርቱ ማስነዋል ፡ ሳቅ እና ሀዘን በፊታቸው ላይ ፍንትው ብሎ ታይቷል መገረምም





መደነቅም ለእነሱ ባይተዋር አይደለም። ግና ያ ቀን ከፉባቸው.... ! በደህናው በትምህርቱ ሰዐት ያስተማራቸውን መክሮ የዘከራቸውን ከልብ ስላላጡኦት በፈተና ወቅት መመለስ የማይችሉት ጥያቄም ትልቅ ፈተናም ሆነባቸው።

አሳልፋ የምትሰጠዋ ነብስ ከጀሌዎቿ ጋር ሆና ታልፋ በምትሰጥ ነብስ ፊት ተሰየመች ። ደቀመዛሙርቱም ተስፋቸውን ፡ ደስታቸውን ሲወሰድባቸው ሲነጠቁ ታወቃቸው ፈሩ ልባቸው ራደ በፍርሃት ባህር ውስጥ እሩቅ ሰጠመ ። ጥርሶቹን መክደን ደስታውን አሳልፎ መስጠት ያልወደደው ጴጥሮስ በማልኮስ ጆሮ ላይ ሰይፍ አሳረፈ ። ግና ጥርሶቹ ዳግመኛ መሳቅ አልቻሉም ፤ የደቀመዛሙርቱ ፊት ለመፍካት አልታደለም። ሁካታው ከፍ አለ ስፈራውን አናወጠ ፤ ‹ስቀለው ስቀለው› የሚሉ ድምፆች ከብዙዎች ፈለቁ ተስፋቸውን ወሰዱት ። በፍርድ ገመድ ጠፍረውት ከሄሮድስ ፒላጦስ ክፉኛ አንገላቱት ። የደም ላብ አላበው ቁና ቁና አቃሰተ ፤ እግሮቹ ሸቅቡን

መውጣት አቃታቸው ለሰስት አመት ተኩል ሰማዩ ፈክቶ ዝናብም አጥተዋል። ሰማዩም አኩርፎ ከፀሃይቱ ጋር ቂያሜ ውስጥ ገብተዋል።

የዛሬዋን ቀን ግን ከቶ አልጠበቋትም ፡ ተስፋቸው የትዬለሌ ያክል ከእነሱ ራቀ እሩቅ ተሰደደ። አይናቸው ያረፈባቸውን ውዳቸውን ሲገርፉት መመልከት፤ እሩቅ ያሻግረናል ብለው ያሰቡትን መሲሀቸውን እንጨት ተሸክሞ እንዝፍ እንዝፍ እያለ ሲሄድ ማየት ፡ ከህመምም የከፋ ትልቅ ህመም ሆነባቸው። የማሪያምን ልጅ እርቃን ገላውን በሚስማር ቸንከረው ሲሰቅሉት መመልከት ያልጠበቁት አበሳ ሆነባቸውና ህመማቸው ታመመ፤ እንባቸውም አነባ ።





## ያነቡ እንባዎች እራት

ትዝ ይሉሻል ውዴ ፡ እነዝያ አመታት፤

ትዝታን የሸመቱ ፡ እልፍ አላፊ ጊዜያት፤

ዳቦ አስደፍተን

ኬክ እየቆረስን

ሻማ እያበራን

እግዜር ጤና ሰጥቶሽ ፡ ልደትሽ ይደርስና፤

ደስታዬን እሰጥሽ ነበር ፡ ከውስጤ ቀዳና።

ሻማሽን እያየው ፡ ፍቅርን ስገልፅልሽ፤



Scanned with CamScanner

አበባ ቆርጬ ፡ ወስጄ ስሰጥሽ፤

በሳሩ ስንደዶ ፡ ቀለበት ሳስርልሽ፤

የሚያምረው አይንሽ ፡ መልስ ይሰጠኛል፤

ለእኔ ያለሽን ፍቅር ፡ በጥልቅ ያሳየኛል ።

ግና ይህ ሁላ ጠዋት ፡ ላይ ነበረ፤

ቀትር ላይ አይሎ ፡ ፍቅራችን በረረ፤

የፈራውት አልቀረም ፡ ልደትሽ ደረሰ፤

እግዜር እቅፍ እንደሄድሽ ፡ አላምንም ያለው ልቤ፤

ይሄ የለመደው ፡ አላርፍ ያለው እጄ፤

ወደ አንቺ ይደውላል...

መልካም ልደት ሊልሽ ፡ በፅኑ ይፈልጋል ፡

ዛሬም በልደትሽ ፡ ስልክሽ አይሰራም ።

ስምሽን ሚጠራ ፡ ከቶ አይሰማም ።





አሁን ገነት ትድመቅ

በሳቅ በእልልታ ፡ ሰማያት ይናወጥ ፤

የማሪያም ልጅ ላንቺ ፡ ዘውዱን ያጥልቅልሽ ፤

መልአክቶች ይነሱ ፡ መለከት ይንፉልሽ ፤

በአብርሃም እቅፍ ያሉ ፡ የአዳም ዘር ሁሉ ፤

መልካም ልደት ብለው ፡ ላንቺ ይዘምሩ ፤

እልፍ አላፍ ኮከብ ፡ እንደ ሻማ ይንደዱ ፤

አንዳንዴም ካሻቸው.....

በግ ሎም እያሉ ፡ አንዳች ውበት ይስጡ ፤

እግዜር ከወደደ ከሰማይ ገፅ ላይ ፡ ኳክብቶችን ወስዶ ፤

እስትንፋሱን ሳያስቀር ፡ እንደ እሳት ማግዶ ፤

ልክ እንደ ምጣድ ፡ ጨረቃን ተጠቅሞ ፤



Scanned with CamScanner

ዳቦውን ይድፉልሽ ።

የኔ ውዱ ጌታ ፣ ፍቅርዬን አደራ ፤

ዛሬ ልደቷ ነው ፣ ከቶ አትከፋ ፤

ከድግሱ መሃል እኔን ስታጣ ፣ ቶሎ ትከፋለች ፤

እንባዋ ቅርብ ነው ፡ እየዬ ትላለች ፤

አደራ ጌታዬ አልመጣም ፣ ከቶ አትበላት ፤

የሰፉን ስንደዶ ፡ አበባ ፍለጋ ፤

ምድር ወርዷል በላት ።

ልክ እንደ ትላንቱ ፡ ዛሬም እንደምወዳት ፤

በዳቦው ላይ ፣ አድምቀህ ፃፍላት ።





## ያነቡ እንባዎች እምስት

ዕለቱ ሰንበት ነው ሀዋሳ ገብርኤል ቤተስክያን እንደወትረው በነጩ ነጠላዎች ደምቃለች። አንዳንዱ ወደ ውስጥ እየዘለቀ ሌላው ቀጤማውን እንደጨበጠ ተሳልሞ ጥድፍ ጥድፍ እያለ ከደጅ ይመለሳል ፤ ገሚሱም ሞተሩን ፡ መኪናውን እያቆመ በሩቁ ይሳለምና መንገዱን ይቀጥላል ። ከውስጥ የሚሰማው የዜማ እና የፀሎት ድምፅ ነብሲያን ይገዛል ስሜት ይገዝታል ። በራፉ ላይ ሆነው መስቀል ፡ የአንገት ክር ፡ ጧፍ እና የመሳሰሉትን የሚሸጡት ልጆች ሃሳብ ይሰርቃሉ። ቤተስክያን ውስጥ ከጥላ ስር ተቀምጠው አንዳች ነገር የሚያወጉት ቄሱና እና ትንሹ ልጅ ይህን ሁሉ ኩነት የታዘቡ አይመስሉም።

ልጁ ይጠይቃል ቄሱ ይመልሳል የትንሹ ልጅ ጥያቄ ማለቂያ ያለው አይመስልም ፤ ዝም ብሎ እንደ ጅረት ይፈሳል።

ልጅ ፡ አባ

ቄሱ ፡ አቤት ልጄ

ልጅ ፡ እንብተህ ታውቃለህ ?

ቄሱ ፡ እንባ የት ይጠፋል ብለህ ነው ልጄ!

ልጅ ፡ ምን ስትሆን ነው የምታነባው ?

ቄሱ ፡ ሆድ ሲብስህ አንዳንዴ በሰውኛ ያልጠበከው እና ያላሰብከው ነገር ሲገጥምህ ውስጥህ ያዝናል ። ታዲያ የዛኔ ብልህ ከሆንክ እንዲያግዝህ ፈጣሪህን እየተማፀንክ ወደ እሱ ታነባለህ ይህን ካልወደድክ ደግሞ በርህን ዘግተህ ለውስጥህ በለሆሳስ ወይም ድምፅህን ከፍ አድርገህ ታነባለህ ።





ልጅ ፡ አባ

ቄሱ ፡ አቤት ልጄ

ልጅ ፡ ፈጣሪሳ ያነባል ?

ቄሱ ፡እስኪ ይህን ጥያቄ አንተን ልጠይቅህ ምን ይመስልሃል ?

ልጅ ፡ እኔ የሚያነባ ይመስለኛል

ቄሱ ፡ እንዴት ?

ልጅ ፡ እሱን ስናስከፋው ፡ ትዕዛዙን ስንተላለፍ ፡ አድርጉ ያለንን ሳናደርግ ስንቀር ፡ አታድርጉ ያለንን ደግሞ ስናደርግ ያዝንብንና ያነባል።

ቄሱ ፡- ጎበዝ ልጄ ! ልክ ብለሃል



Scanned with CamScanner

ልጅ፡ አባ

ቄሱ ፡ አቤት ልጄ

ልጅ ፡ ሰይጣንስ ያነባል ?

ቄስ ፡ አንተ ምን ይመስልሃል ?

ልጅ ፡ ውሃ ልማት መቼስ ውሃ ጠፍታለች ብሎ ሀይላንድ አይገዛ

ቄሱ ፡ ይህን ደግሞ ማን አስተማረህ ?

ልጅ ፡ የሰፈራችን ባለሱቅ ሲል ሰምቼ ነው ፡፡





## ያነቡ እንባዎች ስድስት

ማልቀስ እና ማንባት ፍካሪያቸው አንድ ግን በስያሜ ብቻ ይለያያሉ ብዬ አላምንም፡፡ ማልቀስ የአይን ተግባር ሲሆን ማንባት ደግሞ የልብ ይመስለኛል፡፡

በተረታችን ላይ እናቱ የሞተችበት እና ገበያ የሄደችበት እኩል ያለቅሳሉ ሲባል የሞተችበት ዳግም እንደማትመለስ እያሰበ እንደ ወትሮው ፀጉሩን እያሻሸች እንደማታስተኛው ትውስ ትውስ እያለው ልቡ ክፉኛ ይደማል ፤ ያነባል ፡፡

ያኛው ደግሞ ድው! ቷ! ገጭ! የሚያደርጉትን የታላላቆቹን ኩርኩም እየፈራ የእናቱን መምጣት

እየናፈቀ አይኑን ያስለቅሳል ። አንዳንድ ሰው እየሳቀ ሽንኩርት እየላጠ እየከተፈ ያለቅሳል ።

ገሚሶቹም በአንድም በሌላም ልባቸው ተጎድቶ ሀዘንን አርግዘው ውስጣቸው ያነባል ። ያነባም ላያለቅስ ይችላል ውስጡ በሀዘን ተጎድቶ ለቅሶ የራቀው ብዙ ሰው አለና። የአይን ብርሃን የራቃቸው ብዙ ጊዜ ለቅሶ ሲከዳቸው እናያለን ፡ ቢሆንም ልባቸው ግን የእንባ እንባ ያነባል ። ለእኔ ከማልቀስ ማንባት ይበልጥብኛል። በዚህ ውስጥ ግን ያለቀሰ ሁሉ አያነባም፤ ያነባም ላያለቅስ ይችላል፤ ውስጡ በሀዘን ተጎድቶ ለቅሶ የራቀው ብዙ ሰው አለና። ከልብ ካለቀሱ እንባ አይጠፋም የሚለው ተረት ከልብ ካነቡ ለቅሶ ከአይን አይጠፋም በሚለው ይያዝልኝ ለሁሉም ነገር ምንጩ ልብ ነውና ።





## ያነቡ እንባዎች ሰባት

ከኪሴ ማትጠፉ ፡ ትንሿ መሃረቤ ፤
ከፍጥረት ምትቀድም ፡ የእንባዬ አባሼ ፤
ሰላሜ ሸሸቶብኝ ፡ ብነግርሽ ህመሜን ፤
ምነው ያለወትሮሽ ፡ አባሸው እንባዬን ።



Scanned with CamScanner

## ያነቡ እንባዎች ስምንት

### በጴርጋሞን ገበያ

.......ምንም አዲስ ነገር የለም የጴርጋሞን ደሴት እንደ ቀድሞው በንግድ አሽብርቃለች ።

ጭነት የተሸከሙት አህያዎች የአዛዦቻቸውን ጅራፍ ሳይጠብቁ ሽቅቡን ይወጣሉ፤ ይወርዳሉ ። በጥምጣም ያሸበረቁ የጴርጋሞን ሰዎች በኮሮጃቸው ውስጥ የሞሉትን ሳንቲም በቀራጮች ፊት ይደፋሉ ። ያለወትሮው በየ ጥጋቱ ተቀምጠው የሚለምኑ የኔ ቢጤዎች እንብዛም አይታዩም ። የወጪ ተራማጅ የገዢ እና የሻጭ ክርክር





የነጋዴው እና በየ ጀኒያው የሰፈረውን እህል ለመብላት ከሚንሰፈሰፉ የሰማይ ወፎች መከከል የሚታየው ክስተት ጴርጋሞንን በቀድሞው የኑሮ ዑደት ውስጥ ከቷታል ። ድንገት የጥሩንባ ድምፅ ተሰማ ! ትንሿን ጴርጋሞንን አስተጋባ ። ያኔ ነጋዴውም ዝም ፡ ከሊህቅ እስከ ደቂቅ ፀጥ ፈጭ አሉ። ትኩሳቷ ለአፍታ ተገታ፤ ዝምታም ዝም ! አለ የሚያወራ የለም፤ መለፈፍ ሚፈልግ ከቶ አይታይም። ለነሱ ጥሩንባ የንጉስ ድምፅ ነው። ታዲያ የንጉስን ድምፅ የሰማ ቀልቡን እና ጆሮውን ወደ ድምፁ ይቀስራል ፤ የያዘውን ስራ ይተዋል ፤ በአፉ የገባውን እህል ሁላ ሳያላምጥ እዛው ያቆያል ፤ ጥሩንባው ድምፅ ዳግም ተደገመ። ጡ...ጡ....ጡ.....ሁለት ሶስት ጊዜ ጥሩንባውን እንደነፋ የንጉስ አላስ አዋጅ ነጋሪ መልዕክቱን ሊለፍፍ ጎሮሮውን መጠራረግ ጀመረ። ህዝቡም አንዳች ነገር ለመስማት ጆሮውን ቀሰረ ።

«አዋጅ ... አዋጅ .....አዋጅ.....አዋጅ....የተከበራችሁ እና የተወደዳችሁ የግዛታችን ነዋሪዎች ታላቁ ንጉሳችን ንጉስ

አላስ በዛሬው ዕለት ወደ ደሴታችን በስተ ምዕራብ እና በስተ ምስራቅ በኩል እየተመመ እየገባ ያለውን የጠላትን ወረራ እንዲያከትሙ የጦር ጀግናውን እና መቼም ቢሆን እጅ የማይሰጠውን የጦር ሰራዊታችንን ለዘመቻ ለመላክ የሽኝት ስነ ስርዐት ስላሰናዳ ሁላችሁም ከህፃን አንስቶ እስከ ሽማግሌ ያላችሁ በስነ ስርዐቱ ላይ እንድትገኙ ተብላችኋል ። ያልሰማ ይስማ የሰማ ላልሰማው ያሰማ አዋጅ አዋጅ አዋጅ……አዋጅ…» ያለመታከት ጥሩንባውን ደጋግሞ ነፋና ወደ ተሰበሰበው ህዝብ ዘልቆ ገባ ። ንዴት ፡ ቁጣ ፡ የጀግንነት እና የአሸናፊነት ስሜት በህዝቡ ላይ አስተጋባ ! ሻጩም የሸጠውን ይዞ ሸማቹም የሸመተውን እንደታቀፈ በነቂስ በንጉስ ስርዐት ላይ ለመታደም እየተክለፈለፈ ወደ ጎጀው አመራ።





## ጴርጋሞን በሽኝት ላይ

የጴርጋሞን ቤተ-መንግስት በሰው ተጨናንቋል። የንግስና ካባውን የለበሱ ንጉስ አላስ በዙፋን ወንበራቸው ላይ ከንግስታቸው እንዲሁም ጌጠኛ ልብሳቸውን ከለበሱት ከአልጋ ወራሻቸው ከርከስ ጋር እና ከመጨረሻ ሴት ልጃቸው ጋር በመሆን በስልጣን ወንበራቸው ላይ እንደተሰየሙ ፡ የመጣውን ሰው በአይናቸው ይቃኛሉ። ሁሉም ሰው ላይ የደስታ ፡ ድል የመንሳት ስሜት ፍንትው ብሎ ይታያል ፡ ይነበባል እንኳን ለወዳጅ ለባዳም ያሳብቃል ። የእራት ግበዣ ላይ ያልታደመ የለም፤ ከሊህቅ እስከ ደቂቅ ሁሉም ተሰብስቧል ። የቀረበላትን ማዕድ ይቆርሳል ይጎርሳል ። ካጠገቡ ከተቀመጠው የወይን መጠቻ ኩባያውን እንደ ጨበጠ ይስቃል።

በአዳራሹ ጥግ እሳት እየሞቁ ከሚያዜሙ እንስቶች የሚወጣው ዜማ ለቤቱ አንዳች ውበት ስጥቶታል ። በግራ እና በቀኝ ከተደረደሩ ወታደሮች የሚወጣው ሳቅ



Scanned with CamScanner

የጊቢዣውን አላማ ወደ ድግስ ለውጦታል። በግብዣው ላይ አንድ ምስኪን ወጣት ፊቱ የወየበ ዘወትር ከእጁ የማትጠፋውን ማህደሩን እንደታቀፈ የመጣውን ሰው ለማስደሰት ላይ ታች ይላል ፤ ጥድፍ ጥድፍ እያለ አንዴ ወዲህ አንዴ ወዲያኛው ጥግ ያማትራል ።

ድንገት ሙሙካን የሚል ድምፅ ሰማ፤ የጓደኛው ቆርኖሊዮስ ድምፅ ነው። ሙሙካን አይቶት ፈገገ ።

የወይን መጠጫውን በግራ እጁ በአንዴ ብድግ አድርጎ ድገምልኝ የሚል ፊት አሳየው ።

ሙሙካን በንጉስ ኦሊያስ ግዛት ውስጥ የወጥ ቤት እና የወይን አሳላፊዎች አለቃ ነው ።

የሚባለውን ነገር ጥርት አድርጎ የሚሰማ ግና መናገር የተሰነው ነው። ለጓደኛው ቆርኖሊዮስ ወይን እንዲቀዳለት ለአንዷ አሳላፊ በጠቋሚ ጣቱ ምልክት ሰጣት ። አሁንም የጽርጋሞን ውበት ድምቅ ድምቅምቅ ብሏል።





በሀገራቸው በህል መሰረት ጥበበኞች ግብዣውን አደመቁት። የንጉስ ኦላስ ጥርሶች ፈገግ ማለት ጀመሩ ። ነገሩ ሚስጥሩ ላልገባው ጴርጋሞን ለዘመቻ የምትሄድ ሳይሆን ከዘመቻ ድል ነስታ የመጣች ነው የምትመስለው። ፡ ንጉስ ኦላስ ቀኝ እጃቸውን እያነሱ በተቀመጡበት ብሉልኝ ጠጡልኝ እያሉ ከወንበራቸው ብድግ አሉ ። ያኔ ሁሉም ነገር ድንገት ፀጥ አለ። አይኖች ወደ ንጉስ ኦላስ አተኮሩ ፡ ጆሮዎች ኮቴያቸውን እየተከተሉ ንጉስ ኦላስ ስር ወደቁ። አንዳንዱ የወይን መጠጫውን መሬት ላይ አስቀመጠ ፡ ሌላው እንደ ግራ ጎኑ አጥብቆ ጨበጠ ። ንጉስ ኦላስ የወይን መጠጫቸውን እንደያዙ የመድረኩ የፊተኛው መስመር መሃል ላይ እንደቆሙ በአይናቸው ህዝባቸውን ከገረፉ በኋላ ጎሮሯቸውን ጠራርገው ንግግራቸውን ቀጠሉ። « ህግ እና ስርዓትን የንግስና ወጉን እና ደንቡን የምታውቁ ጥበበኞች፤ በመንግስቴም ቀዳሚዎች የሆናችሁ ባለመዋሎች፤ በህቡዕ ያለውን ወደ ጋሃድ የምታመጡ መፅሃፍ ገላጮች፤ የሁሉም አከባቢ



Scanned with CamScanner

መሪዎች እንዲሁም ከአጎራባች ሀገራት ተወክላችሁ የመጣችሁ ሼታር ፡ አድማት ፡ ተርሸስ ፡ ሜራስ ፡ ማልሰርንን ጨምሮ እንግዲህ ዛሬ ጋሻችን የሆነውን ታላቁን የግዛታችንን የጦር ሰራዊት ወደ ሀገራችን በስተ ምዕራብ እና በስተ ምስራቅ በኩል እየተመመ እየገባ ያለውን የጠላትን ወረራ ጠብስቀው እንዲለቁ ለጦር ሰራዊቴ መንገዳቸው እንደ ማለዳ ፀዳል ብሩህ እንዲሆንላቸው በወይን ቅራሪ እንትፍ ብለን እንድንሸኛቸው ወደዚህ ታላላቅ ውሳኔዎች መወሰኛ አዳራሽ እንኳን በደህና መጣችሁ።» ህዝቡ ፉጨቱን እና ጭብጨባውን አቀለጠ ። « ከዚህ ቀደም ይዘከር እና ይነገር እንደነበረው ብዙዎች እናት ሀገራችው እንዳትሞት መልከ ቢስ ሆና ከስላ እና ደቃ እንዳትቀር ደማችውን አፍስሰው ፡ አጥንታቸውን ከስከሰው ስጋቸውን በቁስል አትመው ፡ እንዴት ሰንደቃችውን ከፍ እንዳደረጉት ከዕይታችን የተሰወረ አይደለም ። ዛሬም ወደ ግዛታችን እየዘለቀ ያለውን የጠላትን ወረራ ድባቅ እንድንመታ





ከሀፃን እንስቶ እስከ ሽማግሌ ፡ ከአሳላፊ እስከ ሹማምንት ያላችሁ በዚህ ዘመቻ ላይ በየ እምነታችሁ ሱባኤ ግቡና የፀሎት ቋጠሮ ወደ አምላካችህ እንድታቀርቡ በአክብሮት እጠይቃለው።» አለና የተሰበሰበውን ህዝብ በፈገግታ አየ ቀድሞ የቆመው ጭብጨባ እና ፉጨት ቀጠለ። «እንግዲህ የዚህ ዘመቻ መሪ ጦር ሰራዊት የሆነው አልጋ ወራሽ ከርከስ ወደዚህ መጥቶ የብዙዎች የደም ውጤት የሆነውን ሰንደቃ ይረከባል ። » አለና አይኖቹን ወደ ልጁ ሰደደ፡፡፡ የተሰበሰበው ህዝብ ተለማምዶት የመጣ ይመስል እኩል ብድግ አለ። ከርከስ ጌጠኛ ልብሱን እንደለበሰ በፈርጣማ ክንዶቹ ብረት እንዳጠለቀ ያ ጠንበለል ጦረኛ በሁለት እርምጃ ከአባቱ ፊት መጥቶ ተደቀነ፡፡

የንጉስ እላስ አማካሪዎች ግዛቱ በጭንቅ ሲዋጥ ብቻ የጦር መሪው ይዞ የሚወጣውን ወርቃማ ጎራዴ በግዛቱ ዱላዊ በመባል የሚታወቀውን ቀስት ይዘው መጡ ።



Scanned with CamScanner

ንጉስ አላስም ወርቃማውን ጎራዴ እና ዱላዊ ቀስት ለከርከስ ሰጠ ::

ያኔ የአልጋ ወራሽ ከርከስ አይኖች አበሩ ፤ፍም ለበሱ :: እጆቹ ተንቀጠቀጡ ጠላቶቹ ከፊትለፊቱ መጥተው የተደቀኑ መሰለው የአባቱን ግዛት እናፈርሰዋለን ያሉትን እነዚያን ቱሪናፋዎችን እነቅ ግደል ከምድር አፈር በታች አድርግ አሰኘው ::

በጉልበቱም በርከክ አለና ከአባቱ እጅ በክብር ተቀበለ:: ጎራዴውን ወደ ሰገባው መልሶ ሰፊውን ህዝብ በአይኖቹ እየገረፈ የጀግንነት ስሜት ሊያጋባባቸው እየሞከረ ወደ አባቱ ዞር አለና «ጀግናው አባቴ የጀግንነትን ጎህ የቀደድክልኝ ምንም ስጋት አይግባህ ጠላቶቻችንን በገቡበት ገብተን ድራሻቸውን እንደምናጠፋ በጼርጋሞን ደሰት ውስጥ በተከሰከሰው በአያቴ አጥንት እምልልሃለው ቃሌም ቃል ነው:: ቃል በሰማይ ቃል በምድር!» አለና የአባቱን እጅ ሳመ::





ጀግንነትን «ለውቃለሁ! እተማመንብሃለው! ልጄ... በልብህ ፅለት ላይ በቀለም ሳይሆን በአባቶች የደም ውጤት ነው የፃፍኩት:: ለዚህ ደግሞ በልብህ ላይ የሚነበበው ምስክር ነው! በድጋሚ ተጋበዙልኝ ወዳጆቼ :: » ብሎ በቀኝ እጁ የያዘውን ወይን ብድግ አደረገ፤ ግብዣውም ቀጠለ :: በቤቱ ጥጋት ላይ ተቀምጠው ሲያዘሙ የነበሩት እንስቶች ማዜማቸውን ቀጠሉ፤ ሁካታው በረታ ጭፈራው ደራ::

## ሙሙካን ሲፈተን

ዘወትር ከእጁ የማትጠፋው ማህደሩ ካጠገቡ ናት:: ከወትሮው የተለየ ስራ ይዟል፤ ሙሙካን በስራ ተጠምዷል:: ሚስማር ይመታል፤ እንጨት ይመግዛል፤ ላቡ ተንቸፍችፏል፤ ልቡ በአፉ ልትወጣ ምንም አልቀራትም! ቁና ቁና ያቃስታል፤ ኮቴዋን ሳታሰማ ሰተት ብላ ከአጠገቡ መጥታ ቆመች፤ ቀድሞ ያየው ጥላዋን

ነው፡፡ ድንገት ቀና አለ ንግስት ራድፍም ናት አይን ለአይን ተጋጩ፤ አየችው አያት፤ ፈገገች ፈገገ፤ ከነገጠኛ ልብሷ ከነ ክብሯ እታች መሬት ወርዳ ካጠገቡ ቁጢጥ እንዳለች «ሰላም ነህ? ሙሙካን» አለችው ፡፡ ደህና መሆኑን ተቋጥሮ የሚፈታውን የግንባሩን መስመር እየተጠቀመ በምልክት መለሰላት፡፡

«ታውቃለህ ሙሙካን ስለ አንተ ሳስብ ሁሌም ይገርመኛል፡፡ በቤተ- መንግስታችን ውስጥ ካሉት ሰራተኞች ስለ እውነት ትለያለህ በዛ ላይ ደግሞ ታታሪ ነህ ፡፡ ብዙ ጊዜ ሁሉም ወደ ታላላቅ ውሳኔዎች መወሰኛ አደራሽ ሲሄዱ እኔ ከአንተ ጋር ለመሆን እመኝ፡በብርቱ እሻ ነበር ፡፡ ለምን እንደሆነ ታውቃለህ ? ብዙዎች ጦር ሜዳ ሄደው ባላንጣዎቻቸውን ይረቱና በንጉሳችን ፊት ጀግና ይባላሉ፡፡ አንተ ድግሞ ሳትጠየቅ ሳትታዘዝ ትሰራለህ የሌላውንም ልፋት ትለፋለህ እንዲህ ሆንኩ እንዲህ አደረኩ አትል ብቻ የቤት ውስጥ ጀግና ነህ» ብላ ዳግም ፈገግ አለች፡፡ አፀፋውን በፈገግታ መለሰላት ግን ፈርቷል፤





ጨንቆታል፤ ግራ ተጋብቷል፤ ነብሱ በአፉ ልትወጣ ተቃረበች፤ ከፍርሃት ጋር የፍጢኝ ተፋጠጠ፤ ከቀድሞው ይልቅ ወደ አጠገቡ ቀረበች፤ አይኗን በአይኑ ላይ ተከለች፡፡ «የአንድ ነገር ውድነቱ የሚታወቀው ተገልጋዩ በሚሰጠው ቦታ ነው፡፡ ምንም ያክል በሌላው ዘንድ ተፈላጊ ቢሆንም ባለቤቱ ጋር ካልከበረ ያ ውዳቂ እቃ ነው፡፡ አሁን አሁን እኔም እንደዛ የሆንኩኝ መሰለኝ፡፡ በእርግጥ ንጉስ አላስ በዚህ ግዛት ውስጥ እንደ ጌጡ እንደሚመለከተኝ አውቃለው፡፡ ግና የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ህግ ሊያመልጥ እንዴት ይቻለዋል? ሁል ጊዜ በሱ እቅፍ ውስጥ መሆንን ትኩስ ትንፋሹ እኔነቴን እንዲስበኝ ፀጉሬን እየደባበሰ በስሜት ግለት እንድንወድቅ እና በፍቅር እንድንሰክር በፅኑ እፈልጋለሁ፤ ግን ምን ያደርጋል እሱ ጋር የለም ሁሌ የሚታየው ጦርነት ውግያ ስልጣን ኤጭ…»

ሙሙካን አሁንም ዝም አለ ዝምታን መረጠ፡፡ ለምን እንደምትነግረው ግራ ገብቶታል ሊያፅናናት ሊያባብላት አልቻለም፡፡



Scanned with CamScanner

« በቃ ዛሬን ብቻ ከእኔ ጋር ሁን ዘወትር እንዲነኩኝ እንዲዳብሱኝ የምመኛቸው እነዚህ ሃለንጋ ጣቶችህ በሰውነቴ ላይ ይረፉ፤ ጡቶቼን ይዳብሱት፤ አንተ እና እኔ ብቻ የፍቅርን ዜማ እንቀኝ፤ እመነኝ ይህ ነገር ከአንተ እና ከእኔ አያልፍም።» እጆቾዋን ወደ ፀጉሩ እየሰደደች የፈለገችውን ነገር ፍንትው አድርጋ እያሳየችው።

ሙሙካን በቅፅበት ተለወጠ ያልጠበቀችው ሌላ ሰው ሆነ። ተስፈንጥሮ ተነሳ ማህደሩን መሬት ላይ ጥሎ ሸሸ፤ ራቃት ፤ ያላሰበው ያልጠበቀው ነገር ሆነበት፤ ሰማይ እና መሬት ተገለባበጡበት፤ ምድርን የቧጠጠ ሰማይን ያረሰ መሰለው ትቷት ፈረጠጠ፤ ወደ ማዐድ ቤቱ ወስዶ እራሱን ሸሸገ።

ንግስት ራድፍም ከተቀመጠችበት አልተነሳችም ቾግሯን ሰምቶ የናቃት መስሏት ሰውነቷ ጋለ፤ ነደደች፤ ሴራ መጠንሰስ እንዳለባት አሰበች፤ በስተግራዋ በኩል ዞር ስትል ጥሎት የሄደውን ማህደሩን አገኘች ፤ማህደሩን





ጨብጣ ካባዋን እያስተካከለች እየተክለፈለፈች ወደ ውበት መጠበቂያዋ ክፍል አመራች እና አንዳች ነገር ይዛ ወደ ታላላቅ ውሳኔዎች መወሰኛ አደራሽ እየተክለፈለፈች ሄደች ። ንጉስ አላስ ከሁለቱ አማካሪዎቹ ጋር እና ከሹማምንቶቹ ጋር ሆነው የሰራዊታቸውን እንቅስቃሴ በማጤን ላይ ናቸው። የአደራሹ በር ድንገት ተከፈተ፤ የሁሉንም ቀልብ ሰበሰበ፤ ከአደራሹ ውስጥ ይሰማ የነበረው ድምፅ ለአፍታ ተገታ ።

ንግስት ራድፍም አንዳች ነገር ሆና እንደመጣች ሁሉም ገብቷቸዋል ምን እንደሆነች ለመጠየቅ ማንም አልተቻኮለም ከእሷ ለመስማት ትእግስትን መረጡ። «ንጉስ ሆይ ክብር ለግርማዊነትዎ» ብላ እጅ ነሳች።

« በዚህ በከበረ በአንተ ግዛት ውስጥ ምን ያክል ቦታ እንዳለኝ አውቃለሁ። አንተም ስለ እኔ ያለህን የከበረ ዕይታ አይቶ እንዳላየ የሚሆን በነውር የተጋረጠ አይነ ህሊና የለኝም። ማንም ግዛታችንን ለመንካት ሲያንሰራራ

አያየን ቁ.... ተብሎ እንደምራቅ ጠብታ፡ እፍ ተብሎ እንደ እፉዬ ገላ ፡ እርግፍ ዝርግፍ አድርገን የምንተወው ውል የለሽ ታሪክ የለንም።» ከቀድሞው ይልቅ ግለቷ ጨመረ፤ ሁሉም ግራ ተጋቡ። «እንደው የኔ ጌታ ያንን ትንግርተኛ መሪ በሜድተራኒያን ባህር ዙሪያ የከተሙትን ሀገሮች በጀግንነቱ እና በጦር ሀይሉ እየጠበሰቀ እስከ ህንድ ሀገር ድረስ የያዘውን ታላቁን አለክሳንደርን አወቁት አይደል ? አዎን ከመሞቱ በፊት ተስካሬን የምታወጡት በደም ነው ብሎ ትንቢት ተናግሮ ነበር ይባላል ። እና ትንቢት ተፈፀመ! ታላቁ መሪ የተናገረው ትንቢት ተፈፀመ፤ ዕውን ሆነ ፤ እሱ በሞተ በማግስቱ ጀነራሎች የጦር መሪዎች ግዛቱን ለመውረስ እርስ በእርሳቸው ጦርነት ጀመሩ፤ ተዋጉ፤ ተፋጩ፤ የግዛት ሽሚያ ፍንትው ብሎ ታየ።

ጌታዬ አንቺ ማለት እሷ ነሽ የምትላትን ብዙዎች ስለ ውበቷ ያወሩላትን ክሊዮፓትራን አስታወሱዋት አይደል? ከታላቁ አለክሳንደር አንስቶ በአስራ ሶስተኛው ከቤርተሎሚወስ ከዛ ከታናሽ ወንድሟ ጋር ሆና እንዴት





የንግስና ካባ እንደተጎናፀፈች ይህ በሀቅ ላይ የተመሰረተ ታላቅ እውነታ ነው። የሮም ነገስታቶችን በውበቷ እንዴት አድርጋ ከእግሯ ስር እንዳደረገች እና ውርደትን አልቀበልም በሮም አልሞትም ብላ በግብፅ እራሷን በእባብ አስነድፋ እንደሞተች የታሪኮች ደጀን ነው ። ታዲያ ጌቶች... እርሶ የመንግስቶት ዋልታ ፡ የልቦት ጌጥ አድርገው ሲሸሙኝ አሁን ግን ጌጥነቴ ረክሶ ፡ ዋልታነቴ ወርዶ ፡ እንደ ሴት አስረካሽ ተቆጠርኩ፤ አምላክ በበትሩ ይቅሰፈኝ አባይ የሆነ ነገር እንደማላወጋ ልቦናህ ያውቃል። ተመልከት ይህ ያ የእርሶ ታላቅ ወዳጅ ሚሼል ፓምፔ ከእስራኤል ሀገር ያመጣልኝ ውድ ጌጥ ነው፤ እኔ እራሴን ልበ ቢስ አድርጌ ያስቀመጥኩት ቦታ ቢሳነኝ ለካ ይሄ የራሱ ሊደርግ በማህደሩ ውስጥ ሸሽጎት ኖሯል። ታዲያ ከዚህ የሚበልጥ ስህተት ጥፋት ምን አለ ?» አስተውሎ ላያት በአንድ መድረክ ላይ ትያትር የምታቀርብ ምርጥ ትያትረኛ ትመስላለች። ስሜታቸውን ሃሳባቸውን ተቆጣጠረች። በሁሉም ላይ ቁጣን ጨመረች።

«ዛሬ ንብረታችንን ለመዝረፍ ድክ ድክ ያለ ውሎ አድሮ ሲነጋ ግዛታችንን ለመቀልበስ እንደማይነሳ ምን ዋስትና አለን ?» ንጉስ አላስ በንዴት ሰጠመ ከችኩሉ ባህሪው ጋር ተዳብሎ ንዴቱ አይሆኔ አደረገው ።

«ይህ የንብረት ብቻ ሳይሆን የማንነት የክብር ጉዳይ ነው። እንዳሻው ከግዛቴ እየቆረሰ እየጎረሰ ግን ኢ- ሰብአዊ በሆነ መንገድ ሆዱን ሊቆዝር የሚወድ ቢኖር ተገቢውን ቅጣት ሊቀበል ግድ ይለዋል። ታዲያ የውዴን ክብር ለመንካት እጁን የሰደደውን ያንን ሰው አምጡልኝ» አለ። ከአማካሪዎቹ ሃሳብ ምክር ለመቀበል እንኳን ጊዜ አልሰጠም ፤ በራሱ ሊቀጣው ሊያፋጥጠው ወሰነ። የተናገረው ቃል ወደ ሁሉም ጆሮ ሾልኮ ሳይገባ ወታደሮቹ ሙሙካንን በቅፅበት አንጠልጥለውት እያንገላቱት አመጡት ።

«ያልዘሩትን ለማጨድ የሚቋምጡ እጆች፡ ያልተገባትን ለማየት የቻኮለች አይን፡ ልታነባ እንባዋ ሁላ ሳይቀር





ሊያለቅስ ይገባዋል። በስንዴው መካከል ያሉት እንክርዳዶች ፡ በህዝብ መካከል የበቀሉ አሜኬላዎች፡ ያልተገባቸውን ለመንጠቅ የሚከጅሉ አይኖችን፡ የጴርጋሞን ሌቦች በሚታጠኑበት ጭስ ውስጥ ድፈቁት» አለና ትእዛዙንም ንዴቱንም ሰጣቸው ።

የንጉስ አላስ ቁጣ በአደራሹ ውስጥ የነበሩትንም በድንጋጤ ሞላቸው፤ በፍርሃት አስጠማቸው፤ እራሳቸውን ለውሳኔውም ለነገሩም አስተያየት ከመስጠት እንደ ቆጠቡ ። ብረት ለባሽ ወታደሮች ለሙሙካን ልክ እንደ ማሪያም ልጅ መከራውን አባሱበት። ሰውነቱ ዛለ ፤ አይኖቹ በእንባ ተሞሉ፤ ቁና ተነፈሰ ፤ የልብ ምቱ በእጥፍ ጨመረ፤ አተነፋፈሱ ተቀየረ ፤እርዱኝ ትንፋሽ እያጠረኝ ነው መተንፈስ አቃተኝ ለማለት ፈለገ ፤ መናገር አለመቻሉ ስቃይውን እንዳያስተጋባ እክል ሆነው ።

ዳር ቆሞ ለሚመለከት የሙሙካን ኩኔት ነብሴን አትውሰጂት ገና ናት እያለ ከሞት መልአክ ጋር

የሚያደርገው ፍልሚያ ይመስላል ። የእሱን እንባ የሚመለከቱት አንዳንዶች አዘኑለት፤ ይቅርታ አድርግለት ለማለት ፈለጉ ፣ የንጉሳቸውን ፊት ገረመሙና ጀረባቸውን ሰጡት። ገሚሱም ይበለው ሲያንሰው ነው ይላል። ንግስት ራድፍም የሙሙካንን ስቃይ ስታይ ውስጧ ተረበሸ ያ ጀግንነት ፣ ያ ቡራ ከረዩ ያለ ማንነት ፣ በንጉስ ፊት ደምቆ የታየ ሴትነት ፣ እያየችው ሟሸሸ ፤ውስጧ በቁጭት ተላወሰ። ካባዋ ከሰውነቷ ላይ ሲዛነፍ ሳታስበው እንባዋ ጠብ... ጠብ ....አለ። ንደቷ በአዘኔታ ተቀየረ፤ በጌቴ ሰማኔ በአታክልቱ ስፍራ ክርስቶስ ሲፀልይ አልፎ እንደሚሰጥ እንደሚሞት ለምልክትነት ከአፍንጫው ላይ የወጣው ወዝ በሙሙካን ላይ በአይኑ ተደገመ። በዙሪያው የረበበው ጪስ ወደ ሰማይ ቤት ማስገቢያ መንገድ መሰለው ። ነብሱ ተጨነቀች ፤ መተንፈስ አቃተው ንግስት ራድፍም እየፈራች ፣ እየተርበተበተች በንጉስ እግር ስር ወደቀች ። ለሙሙካን ምህረትን





ተማፀነች ። «ውዴ እባክህ ይሆን ያክል ከተቀጣ ይበቃል እባክህ ማረው ለዛሬ ብቻ እንለፈው» አለችው።

«እማይሆነውን... እኔ ጠላቴ በስተ ምስራቅ እና በስተምዕራብ በኩል ነው ብዬ ስጠብቅ ይሄው ከግዛቴ ጀምሮልኝ የለ።» ንዴቱ አሁንም ጋብ አላለለትም።

« አውቃለሁ አውቃለሁ ውዴ ቀድሞም እንዲቀጣ መላ የዘየድኩት እኔ አልነበርኩ? ለአሁን ብቻ እንለፈው አለች። አይኖቹዋም የከናፍርቷን እንቅስቃሴ እየተከተሉ እየለመኑ ፤በፍርሃት ማቅቀው አፋቸውን የለጎሙት አማካሪዎች የንግስት ራድፍምን ምግባር ሲመለከቱ አቅም ሆናቸውና በይቅርታ እንዲታለፍ ሃሳብ ለገሱት።

ያኔ ሰማቸው ፤ እንዲተውት በጠቋሚ ጣቱ ምልክት ሰጥቷቸው፤ ምንም ሳይናገር መቋጠሪያውን እንደያዘ ወጥቶ ሄደ።

ውሻ ጌታውን እንደሚከተል በስፍራው የነበሩት ከኋላ ከኋላው ተከተሉት። አሳ ከውሃ ውስጥ ወጥቶ ምድር ላይ ለአፍታ ቆይቶ ዳግም ወደ ውሃ ሲመለስ ህይወቱን ለማስቀጠል እንደሚፍጨረጨር ፡ በጭስ የተቆላው ሙሙካን ከቅጣት ክፍሉ አጠገብ ረጅም ርቀት ሮጦ እንደመጣ ሯጭ ሰርክ ይተነፍሳል ፤ ከንፈሩ ደርቋል፤ ቻርጅ ጨርሰው እንደደከሙት የእጅ ባትሪዎች የቦዘዙት አይኖቹ ገርበብ እንዳሉ ፍም መስለዋል።

በንጉስ አላስ እንደተቀጣ በወሬ ነጋሪ የሰሙት ጓደኞቹ እየኳተኑ መጡ ። ሃሳብ ስሜቱን ሳቅ እና ደስታውን የሚጋሩት ወዳጆቹ ደረሱለት። ከሚንፏቀቅበት ከመሬት ላይ አነሱት። አንደኛው እንባ ተናነቀው «አሁንም ደግመው ቀጡህ አይደል? ምንም በማታውቀው የዱላ መዓት አወረዱብህ አይደል? ቆይ እስከ መቼ ?እስከ መቼ ነው ዝም የምንለው? እስክትሞት? አልችልም... አልችልም ..ወዳጆቼ፤ አልቻልኩም ሙሙካን ።





እኔ ግን ቆይ፡ እኔን አያድርገኝ ፡ይህን መንግስት ለመቀልበስ ሴራ መጠንሰስ እጀምራለሁ አትጠራጠር አደርገዋለሁ።» አለ በንዴት ገንፍሎ ።

ያኔ የሙሙካን የዛለ የደከመ ሰውነት በድንጋጤ አቅም አገኘ፤ ብድግ ብሎ በቀኝ እጁ አፉን አፈነው ። ለአፍታ ሁሉም ዝም ጭጭ አሉ ። ጓደኛው የተናገረውን ነገር ማንም እንዳልሰማ ሙሙካን በቀሉ አይኖቹ ዙሪያውን ቃኘ ማንም የለም ተያይዘው ወጡ ።

የእነሱን መውጣት ተከትሎ የንጉስ ፅሀፈ ትዕዛዝ ገባ። የመደንገጥ ስሜት በፊቱ ላይ ይታይበታል። በፍጥነት ስልኩን ለመደወል መታገል ጀመረ፤ እጄታውን በእጁ ተርበትብቶ ፡ተብረክርኮ አነሳ ቁጥሮቹን መታ፤ ትንሽ ፋታ ሰጠ ፤መልስ አጣ ፤ደግሞ ቁጥሮቹን ተጫናቸው።

ጆሮው ላይ እንዳስጠጋ ደግሞ ደጋግሞ አከባቢውን ቃኘ ማንም የለም ።



Scanned with CamScanner

«ሄሎ... ሄሎ ይሰማል ዘት ዘት ዘታር አድምጠኝ ፀሀፊ ትዕዛዝ ኮድ ስልሳ ሰስት ነኝ መረጃ ላቀብልህ ነው ። ይሄውልሕ የንጉስ አላስ ሰራዊቶች በአሁን ሰዐት በስተምዕራብ በኩል በንባበ ሜዳ በባዛን እየተመሩ እናንተን ለመውጋት አድፍጠው እየጠበቁ ነው።

ዘታሪ እንዳትዘናጉ ገምሰው ደግሞ የፋርስ ሜዳን አልፈው በጴርጋሞን ሸለቆ ውስጥ ከንጉስ አልጋ ወራሽ ጋር መሸገው ይገኛሉ። አስተውል ዘታሪ አሁን የንጉስ አለስ ሰራዊቶች የመሰሪያ እጥረት አጋጥሟቸው ከደቂቃዎች በፊት ሙመርተን የጦር መሰሪያዎችን ይዞ ወጥቷል ። ካልተሳሳትኩኝ አሁን በግምት ወግበተር ሜዳ ይደርሳሉ ከቻላችሁ በመንገድ ላይ ለማምከን ሞክሩ ። ደግሞ ስማ ነገሩ እንደ በፊቱ በሚስጥር ይያዝ ክፍያውን በተለመደው ቦታ ከኩሬው ስር ባለው ዋሻ ውስጥ ያንን ድንጋይ አንስታችሁ ሸጉጡልኝ የኔን ሰው ልኬ እወስዳለሁ በል ቻው ቻው ሰው መጣ መሰለኝ ።»





ዝግ ባለ ድምፅ መረጃውን ሰጠና ስልኩን ዘግቶት ወጣ። የንጉስ አላስ የመጨረሻ ልጅ በግብዣው ላይ አባቷ የወይን መጠጫውን በእጁ ጨብጦ ይሆን እንደነበረው እንደ አባቷ ለመሆን ስትሞክር በንጉሱ ግዛት ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለውን የንጉሱን የወይን መጠጫ ብርጭቆ ሰበረች።

ፈራ ተባ ስትል ያ የዛለ ሰውነት እንዝፍ እንዝፍ እያለ የብርጭቆውን ድምፅ ተከትሎ ሙሙካን ይገባል ። እሷም በድንጋጤ ሰጥማለች ። የአባቷን ቁጣ ጠንቅቃ ታውቃለች ። ሙሙካን ደነገጠ ስብሪባሪውን ለመልቀም ሁለቱም ዳከሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ንጉስ አላስ ከርቀት ከአትክልቱ ስፍራ ሆኖ ስህተትን ብቻ አነፍንፈው በሚመለከቱት አይኖቹ ምክተብ አደረጋቸው። ጥድፍ ጥድፍ እያለ መጣ ተከታዮቹ እግሩን ተከትለው ከአጠገቡ ተሰየሙ ።



Scanned with CamScanner

እኔ ከዛ ከውዳቂ ስፈራ አውጥቼህ ጎንህን የምታሳርፈበትን ስፍራ ሳበጅልህ አንተ ግን ባለፈው በንግስቴ አሁን ደግሞ በእኔ መስታወት ውስጥ የራስህን ምስል ለማግኘት ስትንጨረጨር ማንም ለመንካት የማይደፍረውን የወይን መጠጫዬን ሰበርከው።

ያንን ኣእዋፋትን የሚያስንቀውን በከፍታ ላይ የሚበረውን ንስርን ታውቃለህ□ መቼም ቢሆን በከፍታ ላይ እንዳይሄድ በምድር ላይ ብቻ እንዲርመሰመስ የተቀነበበለትን እባብንሳ አወከው? ነብሱን ይማረውና ደሙን በጴርጋሞን ደሰት ውስጥ ደሙን ያፈሰሰው አባቴ በአንድ ወቅት እንዲህ አለ» አሁንም አይኖቹን ከሙሙካን ላይ ሳይነቅል ።

« ንስር በእነዚያ ከባባድ ክንፎቹ ታጅቦ ከመሬት ከባቢ አየር ርቆ ከዕይታ ጠፍቶ ሸው ሸው እያለ ይበራል ይከንፋል፡አንዳንዴ ጠላቱን እባቡን ለመዋጋት ወደ ምድር ቁልቁል ይወርድና በእነዝያ ጥፍሮቹ ወዲህ ወዲያ



ነት በዮዳኒ(@gbw_dan)

Scanned with CamScanner

እንዳይል ሸርክቶ ይይዘውና እየተመመ አበረረ ወደ ግዛቱ ወስዶት እንዳልነበር አድርጎ ያጠቀዋል ያን ጊዜ አባቡ አቅም ያጣል ጉልበቱ ይማቅቃል።

ለምን ከተባለ ከግዛቱ ስለተሰደደ አሁን ደግሞ ሚሆነው ቀርቶ ማይሆነው ሆነና ተረት ተቀይሮ ከንቱ ሆኖ ቀርቶ አንተ በእኔ ግዛት ውስጥ እኔን ለማጥቃት መንገድ ትጠርጋለህ ማነህ ኩርኩርሳ አርባ ጊዜ ጠበስቁት።»

ግርፋቱ ቀጠለ ኤሎህ ኤሎህ ላማ ሳባቂታኒ ሙሙከን
በውስጡ ያለ ይመስላል።

እየገረፋት ከውጪ ድምፅ ተሰማ ያኔ ግርፋቱ ቆመ። የሁሉም ጆሮ ከውጪ ወደ ሚሰማው ድምፅ ሆነ ፤ የንጉስ አልጋ ወራሽ ከርክስ ነው ሌጣ እግሩ ቆስሏል ልብሱ ከገላው ጋር በደም ተላውሷል ።





«አባዬ ጉድ ሆንን አባዬ በጉድ ተዋጥን መሬት ቁና ሆነች ግዛታችን በጭንቅ ተዋጠች፤ እንደዛ ቡራ ከረዩ
እንዳላልን ዛሬ ግን ማቅ ለበስን።

እንደው አባዬ በግዛታችን ውስጥ ጭንብል አጥልቃ ለባላንጣዎቻችን መረጃ የምትሰርግ ጣት እንዳለች ጥርጥር የለኝም እኛ ሀገር ሰላም አማን ነው ብለን ስንከላወስ በማናውቀው ፈጥነት በባላንጣዎቻችን በጴርጋሞን ቀሻ ውስጥ ተጠቃን ፣ ጓድ ሚንጅለን ጨምሮ ብዙዎች አለቁ እኔም ነብሴ ልትወጣ ዛሬ ጊዜዋ አይደለምና በቀሻ በጢሻ እየተደበኩ እየተከለፈለፍኩ ወደዚህ መጣው ። ለዛች ጣት ግን ወየውላት አባቴ ባያደርገው እንኳን መብረቅ እና ነጎድጓድ በአናቴ ላይ ይውረድ የ አርማጌዶን ጦርነት በእኔ ይጀመር አለቃትም። » ከማንም ምንም መልስ ሳይጠብቅ ጣቱን እንደቀሰረ ሸንከል ሸንከል እያለ ወጣ ከንግስቷ ውጭ የተከተለው የለም ።



Scanned with CamScanner

ለሁሉም ያልጠበቁት ሆነባቸው ፣ የጼርጋሞን ቤተ-መንግስት ጋለች ትኩሳቷ በእጥፍ ጨመረ ቋጠር ፈታ የሚሉ የንጉስ አላስ የማንበሩ ሽንተረሮች እስተውሉ ላይ ይነበባሉ ። የለበሰውን ካባ አወለቀና «ከግዛቴ እንዳሻው እየቆረሰ እየጎረሰ ነገር ግን ካባዬን ለገለበው ለዛ ሰው ወየውለት ፣ አምላክ በበትሩ ይምታኝ አልለቀውም ። የሰዶም እና ጎሞራ እሳት በግዛቴ ይምጣ ያቺ ቀስተ ደመና ምልክትነቷ ጠፍቶ ቃልኪዳንነቷ ተሸሮ ግዛቴ በውሃ ትጥፋ አልለቃትም። ቅንብልቻ ውስጥ ይግባ ስልቻ ውስጥ ይሸሸግ ማን እንደሆነ በግማሽ ሰዐት ውስጥ አጣርታቹ እንድትነገሩኝ ይህ ግን ካልሆነ ለ እናንተም ወየውላችሁ»። አላቸውና የአልጋ ወራሹን ኮቴ ተከትሉ ወጣ።

ለአማካሪዎቹ ያላሰቡት ጉድ ያልጠበቁት ዕዳ ሆነባቸው ጨነቃቸው ። ለራሳቸው ማን ይሁን ተባባሉ መልስ ፈለጉ ሰማይም ዝም ምድርም ፀጥ አለች ።





በጼርጋሞን ደሴት በወንበር ላይ ያሉ ሽንቁር ማን እየወጋቸው እንደሆነ ለማወቅ ጓጉ ከየት መጣ ሳይባል አንዱ የሙሙከን ጓደኛ ከአንዱ አማካሪ አጠገብ ቆሞ ጎሮሮውን በረቸሙ ጠራርጎ ፡ «በአንዲት ነገር እንደተጨነቃችሁና ግራ እንደተጋባችሁ አውቃለሁ። በንጉስ ግዛት ውስጥ ጭንብል አጥልቆ ለንጉሱ ጠላቶች መረጃ ማን እንደሚሰጥ ትናጋዬ ከላንቃዬ ይጣበቅ ጠንቅቄ አውቃለሁ።» አላቸው። የሁሉም አይን ወደ እሱ ዞረ ምላሹን ፈልጎ። ተአምረኛው መልአክ ከገቡበት ጉድጉድ ጎትቶ ሊያስወጣቸው ገመድ የወረወረላቸው መሰላቸው። «ይህን ግን የምነግራችሁ እንደ ወጉ እና እንደ ስርዐቱ ስናደርግ ብቻ ነው» አላቸው ክፍያ እንደፈለገ በፊቱ እንቅስቃሴ እየገለፀላቸው። መረጃ አሳልፎ የሰጠው ፀሃፊ ትዕዛዝ የመፍራት የመደንገጥ ስሜት አይታይበትም ። ድንገት ይህ ከተፈጠረ ብሎ ለሙሙከን ጓደኛ በህቡዕ ከፍሎት እሱ የጠነሰሰው ሴራ ጭንቅላቱ የፈጠረው ድራማ ስለሆነ እምብዛም



Scanned with CamScanner

አልፈራም። አማካሪዎቹ ተወያዩና በኮሮጆ አድርገው ትንሽ ገንዘብ ሰጡት ። « በል ንገረን ማነው?» አለ ጠና ያለው ሽሚምንት ፂሙን እያሻሸ ።

«እንዲህ ያለ ሰው ከጥፋቱ ሊታረም ይገባዋል ታዲያ ለጠላቶቻችን መረጃ አሳልፎ የሰጠው በንጉሱ ግዛት ውስጥ ምግብ አዘጋጅ እና ወይን አሳላፊ የሆነው የገዛ ጓደኛዬ ሙሙካን ነው።» አለ አንተን ያለጥፋትህ የሚቀጡህን ያለ ወንጀልህ የሚከሱህን የጼርጋሞንን መንግስት እና ጀሌዎቹን ለመገልበጥ መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ሴራ እጠነስሳለው እንዳላለ ዛሬ ታከተው በገንዘብ ተሸጠ። «ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሙሙካን ለራሱ መናገር የማይችል ሃሳቡን እንኳን ለመግለፅ አቅም የሌለው መረጃ አሳልፎ ሰጠ ለማለት ለእኔ ትንሽ ይከብደኛል።» አለ አንደኛው አማካሪ።

«ያልጠረጠረ አሉ ሊሆን ይችላል ይህ ልጅ መናገር ባይችል እንኳን ሃሳቡን በብራና አድሮጎ በፊደል ከትቦ





በመልዕክተኛ ሊልክላቸው ይችላል። ጓዶች በለፈው የንግስታችንን ንብረት ከማህደሩ ዘንድ አኖረ ቀጥሎም የከበረውን የወይን መጠጫ ሰበረ ወዳጆቼ ንቁ እንጂ »አላቸው ሊያስማማቸው እና ወዳዘጋጀው ድራማ እየመራቸው ፀሀፊ ትዕዛዙ። ሁሉም በሰሙት ነገር ለመስማማት ትንሽ ከበዳቸው በተጨባጭ ያላረጋገጡትን ነገር የወሬ ወሬ ለንጉሱ ለመናገር አልወደዱም ግን ተገደዱ መከረኛው ጣት በአንዱ ላይ ከልተቀሰረ አንዳቸውም እንደማይተርፉ ገባቸው እንደ ማሪያም ልጅ ሙሙካንን አሳልፈው ሰጡ ።

ይህን ነገር ንጉስ ኦላስ በሰማ ጊዜ ስሜቱን ለማስታገስ ቁጣውን ንዴቱን ለማዳመጥ ጊዜ አልሰጠም ከአልጋ ወራሹ ከሰገባው ሰይፍ መዞ የሙሙካን ሆድ ላይ ሰደደው ሙሙካን በሁለት እጆቹ ሰይፉን እንደያዘ ደም እያስመለሰው መሬት ላይ ወደቀ። ከሞት መልአክ ጋር ታገለ አቃተው ደከመ ተሸነፈ።



Scanned with CamScanner

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)
ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)
Telegram Channel



## ያነቡ እንባዎች ዘጠኝ

የጠራ የእግዜር ቤት ፡ ጥርት ያለ ሰማይ፤
ሲስቅ ያስተውላል ፡ ያንጋጠጠ ወደ ላይ ።
የመብረቅ ብልጭታ
የሰማይ ጉርጉምታ
መጣውኝ የሚል ፡ የንፋስ ሽውታ፤
የነጎድጓድ ድምጾች ፡ ከላይ ቤት የሉ፤
ሚራገፉ ቅጠሎች ፡ ከቶ አይታዩ፤
ብቻ ዝም ብሏል፤
ዝምታን መርጧል ።



Scanned with CamScanner

እና በዚች ቀን....

ብዕርህን ጨብጥ ፡ ብራናህን ውጋ ፤

ቀለሟን አስተፋ ፡ እንባዋን አስነባ ፤

እልፍ አዕላፍ ፡ ቃላቶችን ሰድር ፤

ስንኞችን ቋጥር ፡ ፊደላትን ደርድር ፤

ፃፍ ፃፍ ግጥም ፡ ግጠም አሰኘው ፤

በጣቶችህ መሃል ፡ ብዕርህን እነቅ አለው ፤

የራሱ ሃሳብ ፡ እራሱን ረበሸው ፤

ብዕሩን አሰጨብጦ ፤

ከአንዲት ከፍታ ላይ ፡ ሸቅብ አስቀመጠው ።





በሃሳብ ዳከረ፡ በሃሳብ ማቀቀ ፤

ላይ ታች እያለ ፡ ደከመ ደቀቀ ።

ወዲህ ወዲያ እያለ ፡ እሩቅ ተንገላታ ፤

ልክ እንደ ማሪያም ልጅ ፤

ሃሳብ ተሸክሞ ፡ ጎልጎታ ላይ ወጣ ።

የራሱ ማንነት ፡ እራሱን ገረፈው ፤

ቀለሙን ሊያስተፋ ፡ ሀሳቡን ሰቀለው።

እዛ ከላይ ሆኖ እንደ ተሰቀለ ፤

ቁልቁል አጎንብሶ ፡ ሁለት ቤቶች አየ።

እኚህ ሁለት ቤቶች ፡ እንደ ተሰየሙ፤

ከሃሳብ ጎልጎታ ዳኝነት ፈለጉ።



Scanned with CamScanner

በፍርድ ሚዛን ፊት መቀመጥ ፈለጉ

እናም አንደኛው ቤት....

በሩ ተጠርቅሟል ፡ በጋን ተከርችሟል ፤

የጭቃው ምርጊት ፡ መሬት ላይ ወድቋል ።

ቆርቆሮው ቀድ ነው ፡ ጣራው ያፈሳል ፤

ፀሃይን እና ዝናብን ፡ አዋዶ ይኖራል።

አስተውሎ ላየ ቤቱ ፡ ስርዐት አጥቷል ፤

ባደፉ ዕቃዎች ፡ ቅጥአንባሩ ወጥቷል ።

ጭል ጭል የምትል ፡ትንሽ አንፖል አለች ፤

ፅልመት የበለጣት ፡ በርታ ብርሃን ያጣች ።

ቤቱ ያስፈራል ፡ ነፍስ ያስጨንቃል ፤

መንፈስ ይረብሻል ።





በግድግዳው እናት ፡ ያረፈው ምስል ፤

ድር ደርቶበታል ፡ አቧራ ረቦታል ።

ወዲያ....

ሌላ ቤት አለ ፡ ጎልቶ የሚታይ፤

ከቀድሞው ቤት ፡ ፈፅሞ የሚለይ፤

ሳንቃው ተበርግዷል ፡ ግድግዳውን ነክቷል ።

የብርሃን ጭላንጭል ፡ በከፊል ይታያል፤

በራድ አይሉት ትኩስ ፡ ቤቱ ለብ ብሏል።

እኚህን ሁለት ቤቶች ...

ደራሲው ፃፋቸው!

በምናብ ሸራ ላይ ፡ አድምቆ ሳላቸው።

ወዲህ...

በዘመመው ቤት፡ በከርቸም በር ፤

ተስፋ የሸሸው ፡ የህይወት ስንክሳር ፤

ክምር ተሸክማ ፡ እንዲ ታነባለች ፤

እኳላቷን ሁሉ ፡ ጥቁር አልብሳለች፤

ልጄ...ልጄ.....ልጄ ትላለች ።

እንባዋ ያስፈራል ፡እንባዋ ያስነባል፤

ከቤቱ ጋር ሆኖ ፡ ጋሃነም ነን ይላል ፤

ለልጇ ደከማለች ፡ አይሆኑ ሆናለች ፤

ላጣውት ባሌ ፡ ምትኬ ብላለች ፤

መኖር ማለት ለሷ ፡ የሞተው ልጇ ነው፤

ሳቅ እና ደስታዋን ፡ ፈጣሪ የሆነው ።



ያነበ አንባዎት

አሁን እርሱ የለም ፡ ርቆ ሄዶባታል ፤

ሳቅ እና ደስታዋን ፡ ሳይፈልግ ነጥቋታል ።

ጠንካራ ማንነት ፡ ውስጠቱ ተንዷል ፤

አይኔን በአይኔ ያሉት ፡ እየታየ ሄዷል፤

ህይወቷ ጨልሟል ፡ ድንግዝግዝ ብሏል ፤

ስራዋ ማልቀስ ነው ፡ የዘወትር ምግባሯ ፤

እህል አትቋደስ ፡ እንባ ነው ምግቧ ።

ወዲያ...

ከፈካ ሰማይ ፡ ስርክ ከፈገገ፤

በተከፈተ በር ፡ ብርሃን በነገሰ፤

በሌላኛው ቤት ፡ ሌላ ሴት አለች ፤

ልጇን ታቅፋ ፡ እሷን ታነባለች ፤



Scanned with CamScanner

የእናቱን እንባ እየተከተለ ፤

ሀጻኑም ያለቅሳል ፣ እማዬ እያለ ፤

ስሟን እየጠራ ፡ እያቆላመጠ ።

እዚያ...

ነጠላ አዘቅዝቃ ደረት እየደቃች ፤

ለምታነባ እንስት ሙሾ እያወረደች ፤

ማጣት ነው እንባዋ ማልቀስ መጎዳቷ ፤

ሀዘንን ሸልሞ የራቃት ደስታዋ ።

እዚህ...

ማግኘት ነው ሀመሟ ፡ ሳቋን የነጠቃት ፤

ልጇን ታቅፋ ፡ አይሆኑ ያረጋት ።





እኝህን ሁለት ቤቶች ፡ በብዕሩ አያቸው ፤

መልሶ መላልሶ ፡ በደንብ አጤናቸው ።

ለዚያች በዕጦት ነው እንባዋ ፤

ከፉኛ የተጎዳው ፡ የደማው ልቧ ።

ንጋት ሚባል ከሷ ዘንድ የለ ፤

ድንግዝግዝ ጨለማ ፡ በቤቷ ከረመ ።

በጠቆረ ሰማይ ፡ እጅግ በጠለሸ ፤

ኳክብቶች አምፀው ፡ ብርሃን በሸሸ ፤

ዘወትር በሚደግሙ ፡ በእነዚህ ኩነቶች ፤

ከወየቡ ፊቶች ፡ ከቀሉ አይኖች ፤

ጥቁር ከለበሰ ፡ ከጋለ ሰውነት ፤

እጅግ ከተጎዳ ፡ ካዘነ ማንነት ፤



Scanned with CamScanner

በጋን ከተዘጋ ፡ ከተቆለፈ ቤት ፤

ጠብ... ጠብ .... እያለ ፤

ይወርዳል የእንባ ሽንትር ፤

የሞተ ልጇን ይመልስ ይመስል ።

ይህቺ...

ዕልፍ ጊዜ ፈልጋ ፡ ዕልፍ ጊዜ ያጣች ነፍስ ፤

ዕጦቷን ለመሙላት ፡ የማሰነች በየብስ ፤

ከዕለታት ባንዱ ቀን ፡ ፋሲካዋ ሆነና ፤

የነፍሷን ጥያቄ ፡ ፈጣሪ ሰማና ፤

ማህፀኗን ቢከፍተው ፡ አምላክ በታምሩ ፤

ከምስጋና ይልቅ ፡ ለቅሶ ሆነ መዝሙሩ ፤

ዋይታ ሆነ ዲስኩሩ ።





ልጇን ለማግኘት ፡ ብዙ ማሰናለች ፤

ደግማ ደጋግማ ፡ እግብታ ፈታለች ፤

ባል ነን እያሉ ፡ የሚመጡት ሁሉ ፤

ሚስጥሩን ሲያውቁ ፡ ከእሷ ይሸሻሉ ፤

ለልጅ ይመስል የእነሱ ፡ መምጫያቸው ፤

ህመም ብቻ መፍጠር ፡ ሆነ አመላቸው ።

ብዙ ባሎች ያላት፡ እያሉ ያሚታል ፤

ባልኖረቸው ቁና ፡ እሷን ይሰፍሯታል ።

ከሰው ተነጥላ ፡ እሩቅ ተሰዳለች፤

በማታውቀው ምድር ፡ ባይተዋር ሆናለች ።

ልጅ ፍለጋ መታመም ታማለች ፤

እናም ለዚህች ሴት ..

ልጇን መውለዷ ፤

አቅፋ መሳሟ፤

መሻቷን ማግኘቷ፤

ከደስታ ይልቅ ፡ ሀዘኗን ጨመረ፤

የቀድሞ ታሪኳን ፡ ትዝታን ፈጠረ።

በኋሊት ፈረስ ፡ በምልሰት ከነፈ፤

ሀመሟን ተረከ ።

ማግኘት ነው እንባዋ ፡ ሳቋን የነጠቃት፤

ልጇን ታቅፋ ፡ አይሆኑ ያረጋት።

የኻህን ሁለት ሴቶች ፤

የኻህን ሁለት ቤቶች ፤

እዛ ከላይ ሆኖ ፡ እንደ ተሰቀለ ፤





ከሃሳብ ጎልጎታ ፡ እንባቸውን አየ።

ብዕሩን አስለቅሶ ፡ እንዲህ ፃፋቸው

በዚህ አተማቸው ።

ያነቡ እንባዎች

በምናብ ሸራ ላይ ፡ ያነቡ እንባዎች፤

እጅግ የተጎዱ ፡ የህመም ህመሞች ፤

ብዕሮቹ አዩዋቸው ፤

ዳኝነት ለመስጠት ፡ ትንሽ ከበዳቸው።

ስለ ማጣት መፃፍ ፤

ስለ ማንባት መፃፍ ፤

የዕለት ልምዳቸው ፤

መግጠም ነው ስራቸው ፤



Scanned with CamScanner

ግና...

በማግኘትም እንባ ፤ እንዳለ በሀገሩ ፤

ለብዕሮቹ ቀለም ፤ ትምህርት ሆነው ቀሩ ።





## ያነቡ እንባዎች አስር

ነፃነት የለም

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ነፃ ነው ብዬ አላምንም።

በረጅም ገመድ ስለታሰረ ይሄው ከስነ ፍጥረት ጀምሮ ሁሌም ሰው በታጠረለት አጥር ውስጥ ይማስናል፤ በተቀነበበለት ሳጥን ውስጥ ይወላገዳል። ከተፈጥሮ ፡ ከፈጣሪ ፡ ከሰይጣን ፡ ከማህበረሰቡ ሀሳብ ፈቀቅ ማለት አልቻለም። የራሱን ሀ መሳብ አቅቶት ሀሳብ ሳይኖረው ከሌላው ማህበረሰብ የቃረመውን አስተሳሰብ ሰንቆ ይኳትናል ።ለምን ካልከኝ ከላይ ያሰመርኩትን አንብበው!



Scanned with CamScanner

የኛንስ ተወው በወንድ እና በሴት ፈቃድ ፅንስ ለሆኑት ፅንሶች ልዘን እንጂ ፤ ፅንስነታቸው አልፎ ጨቅላ ሲሆኑ በማያውቁት አለም ባልሰፈሩት ቁና ባልኖሩት ባህል ይፈረጃሉ። ከፈጣሪ ሳጥን ውስጥ ለመውጣት ቢጣጣሩም በማህበረሰቡ ሳጥን ውስጥ ይወድቃሉ።





## ያነቡ እንባዎች አስራ አንድ

በኑሮዋ ፋና ፡ ማንም ሳይደርስላት ፤

ህይወቷ ከሰመ ፡ በልጇ <u>ገደላት</u>።



Scanned with CamScanner

## ያነቡ እንባዎች አስራ ሁለት

የጎጆው ጣሪያው ያፈሳል ፤ መስኮቱም በሩም ከበታው ላይ ተነቅሎ ተነስቷል ፤ ዕቃ በየ በታው ላይ ተጥሏል፤ የከብቶች እንበታ እንደ ቀድሞው አይሰማም፤ ከደጅ የሚመጣው የእንቁራሪት ቁረያ እቤት ድረስ ዘልቆ ጎጆውን የገሀነም ጎረቤት አስመስሎታል ፡፡

በዚህች ቤት ውስጥ አንዲት እናት ፀጉሯ ተበታትኗል ፤ የለበሰችው ሸማ ጥለቱ ቅድ ነው፡፡





በጉበኑ ላይ እንደተቀመጠች በትካዜ በሀዘን ርቃ ትሄዳለች ከሀሳቧ ስትባንን ከሰመመን ስትመለስ በለበሰችው ልብስ እንባዋን ታብሳለች ፡፡

እንባዋ ጥልቅ ነው ! በጎጆዋ ደጃፍ እያለፈ የነበረው መንገደኛ የፈረሰውን ቅጥር የዘመመውን ጎጆ አየው ፡፡ ይህን ቤት ያውቀዋል ከአንድም ሁለቴ እያለፈ ውሃ ጠጥቷል፡፡

መዝግያ ባጣ በር በኩል የወደቀ መሰብ አየ ይህንን መሰብ ከዚህ በፊት ያውቀዋል፡ እንደ ቤተኛ ማዕድ ተቋድሶበታል ምንም ሳይናገር የሸከፈውን ሻንጣ ደጅ ላይ አስቀምጦ ዘልቆ ገባ፡፡

ኮቴው ቀሰቀሳት ከሰመመን መለሳት ቀና ስትል ዘወትር ቀዝቃዛ ውሃ እየቀዳች የምታጠጣው ሳይሳለማት የማያልፈው ያ መንገደኛ ነው፡፡

ቀና ብላ ልትስመው ፈለገች ለመነሳት አቅም አጣች፤ ከበዳት «እማማ ሰላም ኖት? ምንድነው ምን ተፈጠረ ቤቱን ማን አፈረሰው ? በሩን መስኮቱን የጣረያውን ቆርቆሮ ማን አፈረሰው? ማን ወሰደው? ልጆቹስ ወዴት ሄዱ?» አለና የጥያቄ መአት አወረደባቸው ። ከማንባት ከማልቀስ ውጪ ምንም መልስ አልሰጠችም ፤ ደግሞ ጠየቃት ተጨነቀ እርሱ የጠየቀውን ጥያቄ መልሰ ለራሱ መመለስ ጀመረ ብዙ ምላሾችን ህሊናው መለሰለት።

አንዱንም መቀበል አልፈለገም ፡ ህመሟ አመመው፤ ጠዘጠዘው፤ ነገሩ ሳይገባው ስሜቷ ተጋባው ሽንቁር ወጋው ፤ወደ እቅፉ አስጠጋት በእንባው መልሰ እራሱ አረጠባት።

«እናቴ እናቴ እናቴ አትበሉኝ እናንተው ቀብራችሁኝ እናንተው ገላችሁኝ እናቴ እማ እናታችን አትበሉኝ አዎን ሙሾው ተደርድሮ እንቢልታ እየተነፋ ነጋሪት እየተጎሰመ ደረት እየተደቃ የሞት ሞቴን እሞታለው፤ እናቴ...





እናታችን አትበሉኝ።» አለች በሰለለ ድምፁ ከቀድሞው ይልቅ ህመሟን ሊረዳ በፅኑ ፈለገ ችግሯን ለመስማት በብርቱ ጠየቃት።

ውስጠቷን ሰርስሮ ልቧን ያደማትን ለማወቅ ቾኮለ «ልጄ የኔንስ ተወው ....

ኑሮዬ ቅድ ነው ፡ ሽንቁር የተወጋ ፤

መንገዱን ስቶ ፡ እድግ የተዛባ ፤

ያንን ትልቅ ጎጆ ፡ መሰረቱን ንደው

ደጅ አሳደሯት..........

ለእነሱ ሚበጀውን ፡ አዲስ ጎጆ ሰርተው ፤

ማገር መሰሰውን ፡ ለራሳቸው ወስደው»።

አለችው በቅኔ የውስጧን ጩኸት እያወጣች ምን ለማለት እንደፈለገች ለመረዳት ብዙም አልተቸገረም።



Scanned with CamScanner

ግን ምክንያቱን ለማወቅ ፈለገ «እንዴት? እማማ ምን ተፈጠረ?» አላት ይህን ጥያቄ ቀድሞ እንደጠየቀ ዘንግቶት «መቼስ ልጄ ቀድሞ የነበረውን የዚህችን ቤት ሙቀት ታውቀው የለ አሁን ግን የለም አሳቱ ተዳፈነ እመዱ ዙርያውን ሞላው ሁሉ ወና ሆነ ከንቱ ባዶ ሆኖ ቀረ ። ጎጆዋችን እንደዚያ ነበር እያሉ የሚያወሩለት እንዳለፈ ታሪክ ተረት ሆኖ ቀርቷል ከመደቡ ስር በጋራ ተቀምጠን ተሰብስበን ማዕዳችንን የምንቋደስባት መሶብ ያው እንደምትመለከተው ነው መሬት ላይ ወድቋል ልጄ ኑሮው ለየቅል ከሆነ ከርሟል ምን አደከመህ ልጄ ውሎ ሰንብቷል። ለማንም ያላወጋውትን የሚሰማኝን እስኪ ለአንተ ላውጋህ ልጄ » አለችውመሬት ላይ ወድቆ አቧራ የሰበሰበውን ነጠላዋን እያነሳች ። «ይንገሩኝ ይንገሩኝ እናቴ» አላት ያነሳችውን ነጠላ አቧራውን እየጠራረገ።

«ዕለቱ ቅዳሜ ይመስለኛል ልጄ አሮጌው ዘመን አልፎ አዲስ ዘመን ሊገባ አንድ ቀን ሲቀረው ። ያ ቀን ልዩ ነበር ከልጆቼ ጋር አሮጌውን ዘመን ለመሸኘት ሽር ጉድ ስንል





አመሸን መልሰው መላልሰው በሚያዜሙት ዜማ የጌንም አርጅና አስረስተውኝ ደግመን ደጋግመን እስክስታ ወረድን ቤታችን ዳንኪራ በዳንኪራ ሆነ። እንደፈማዳችን በቤተሰብ መሶብ ላይ እራቱን አሰናዳው ማዕዱን የሰጠንን ፈጣሪያችንን አመሰገንን ብዙዎች ከመቃብር አፈር በታች ሲገኙ ሌሎች በህክምና ማዕከል በሞት እና በህይወት መካከል ሆነው ሲማቅቁ አንዳንዶችም በህይወት ስንክሳር ውስጥ ተጠላልፈው ሲንከላወሉ እኛን ግን አሮጌውን አመት አሻግሮ ለአዲሱ አመት ያበቃንን ፈጣሪ አመስግነን ማዕዳችንን ስንቋደስ ዳቦዋችንን ስንቆርስ የመጀመሪያው ልጄ በእጁ የያዘውን ጉርሻ ወደ ቦታ መልሶ ብድግ ብሎ ቆመ ቀልቤን ገዛው ሊያወራ የፈለገው ሊናገር የተመኘው ሃሳብ እንዳለ ሊያጎርሰን የሰነቀ ስንቅ እንዳለው አይኖቹ ቀድመው ነገሩኝ።

ቅድም ውስጥህ ተጨንቆ አንተ እኔን እንደጠየከኝ ምን ሆንክ ምን ተፈጠረ ልጄ አልኩት ቶሎ እንዲመልስልኝ አይኖቼን ከአይኖቹ ላይ ሳልነቅል።

እማ እዚህ ቤት ይህ የመጨረሻ ጉርሻዬ ነው ብሎ ቁጭ አለ። እንደ ጌታችን እራት የመጨረሻ እራትህ ነውን ብዬ ወደ ቀልድ ለወስደው ሞከርኩ አልሆነም። እማዬ አዝናለሁ በዚህ መሶብ ዳግም አልበላም አነስ ያለች መሶብ ገዝቻለው ከዚህ ያልበለጠች ትንሽ ጎጆ ለሰራም እናቴ መንገድ ጀምራለው፤ እንደውም ጨርሻለው ስልሽ! እማ ውሸት እንዳይመስልሽ ደጀን ምሰሶውም ሁሉም ቆሟል አሁን የጎደለኝ መስኮት ብቻ ነው። አለኝ ልጄ የሰማሁትን ማመን አቃተኝ እግሮቼ ተብረከረኩ ትንፋሼ ለአፍታ ተገታ ከሳጥኑ ውስጥ መደሻውን አወጣና መስኮቱን መምታት ፤ እንጨቱን መመገዝ ፡ መቁረጥ፡ ሚስማሩን መንቀል ፡ጀመረ ፤ ሁሉም ህልም ሆኖ ታየኝ የጎረስኩትን ጉርሻ ማላመጥ ተሳነኝ፡

አንድን ተራራ የምጓዝ ሸቅብ የምወጣ መሰለኝ። መስኮቱን ነቅሎት ይዞት ሄደ ተመካከረው የመጡ ይመስል አንደኛውም የወንድሙን ዳና ተከትሎ ጉልበቴን ሳመና እሱም በተራው የጎጆዋችንን በሩን ነቅሎ ይዞት





ሄደ። የመጨረሻው ልጄም ከሰው ቤት መሰላል ተውሶ እማዬ ማሪኝ ይቅር በይኝ ድርሻዬን ነው የቃረምኩት እያለ ከጣራው ላይ ቆርቆሮ ነቃቅሎ ይዞ ሄደ።

ይህ ነው እንግዲህ ልጄ ዋናውን ጎጆዎቻውን እያፈራረሱ ጎጆ ሰራን ይሉኛል።

መሰብሰቢያቸውን ሁሉንም አዋህዶ አንድ ያደረጋቸውን ጎጆ መልሶ መላልሶ እያፀኑ አዲሱን ጎጆ ማበጃጀት አይቻልም ልጄ ? የእናታቸውን ጎጆ ማፈራረሱን ምን አመጣው ልጄ ? ለዚህም ነው እንባዬ ያነባው ህመሜ የከፋው። በጥልቅ ከፉኛ የተጎዳው ልቤ ለዚህ ነው ልጄ እናቴ እናቴ እናቴ አትበሉኝ እናንተው ገላችሁኝ እናንተው ቀብራችሁኝ እናቴ እማ አትበሉኝ ለዚህ ነው ልጄ

የኔንስ ተወው ........

ኑሮዬ ቅድ ነው ፡ ሸንቁር የተወጋ ፤

መንገዱን ስቶ ፡ እጅግ የተዛባ ፤

ደጅ አባደራ ፦

ለእነሱ ሚበጀውን ፡ አዲስ ጎጆ ሰርተው ፤

ማገር መሰሶውን ፡ ለራሳቸው ወስደው።

ያልኩት ለዚህ ነው ህመሜ የከፋው እንባዬ ያነባው።»



## ያነቡ እንባዎች አስራ ስድት

ፉታ በማይሰጡ ፡ በህመም ክምሮች ፤

እጃቸ በሚያስነቡ ፡ በችግር ከርችሞች ፤

መሃል ቁጨ ብሎ ፡ ነፍሱ ተጠፍንጎ ፤

ግን እንባ የከዳው ፡ ባይተዋር አድርጎ ፤

ውስጠቱ ቢጠና ፡ ቢጤን ነፍሲያው ፤

የእንባም እንባ ነው ፡ ውስጡ ያለቀሰው ፡፡



Scanned with CamScanner

## ያነቡ እንባዎች አስራ አራት

በሀይወቴ ውስጥ በማይነጥፍ እና በማይደበዝዝ ቀለም ስማቹን እና ሀይወታቹን ያኖራችሁ የአይኔ ብሌኖች ለጤናችሁ እንዴት ከርማችኋል ? የኔዋ ያለ እኔ ኑሮው እንዴት አድርጎሻል? ባቢን ማስጠናት ኩኩሻን ማጥባት እንዴት ይዞሻል ? እማዬም ልጆቹን ለማየት ቤታችን እንደምትመጣ ሰማሁኝ ቤቱ ያለ እኔ ሊውጥሽ እንደደረሰ በዶክተር አሮን በኩል በላከሽልኝ መልእክት ተረዳው:: አውቃለው የኔዋ የኔን ጉርሻ ለምደሽ ምግቡ አሬት አሬት እንዳለሽ አልጋው ከበረዶ በላይ እንደበረደሽ ቤቱ ከገነት መውጫ ወደ ሲኦል ማስገቢያ በር እንደሆነብሽ አውቃለው የኔ አለም ግን ይህን ብቻ አወቂልኝ በእያንዳንዱ ደቂቃ መሃል አስባቹኋለው፤ በየሰከንዱ በእቅፌ ውስጥ ላገኛችሁ እሻለው፤ ግና ምን ያደርጋል





ሀይወት የራሷ የሆነ መመሪያ አላት እኛ በወደድነው እና በመረጥነው መንገድ አንመራትም ። የአሁኑ ችግር እኔን እና እንቺን ብቻ ሳይሆን የአለምን ህዝብ ነው ያስጨነቀው ታዲያ ውዴ ያንችን ከእስትንፋሴ በላይ የምሳሳላቸውን የልጆቼን ሁሌም የኔን ደስታ እና ሳቅ ከፊቴ ላይ ለማየት የምትፈልገውን የእናቴን ብሎም የአለምን ህዝብ ለማዳን ብዬ ስዳክር እና ከመልአከ ሞት ጋር ግብግብ ስፈጥርም አይደል አልጋ ላይ የቀረውት ታዲያ የኔ አለም በሞት እና በህይወት መካከል ሆኜ ለመኖር እየታገልኩ ይህን ስፅፍልሽ እኮ ደስ እያለኝ ነው። ብሞትም የወታደር የጀግንነት ሞት እንደ ምሞት እያወኩኝ እንባዬ በሳቅ ይተካል። በእንባዬ ያበሰበስኩትን መፃፊያዬን መልሼ በክንዴ አብሰዋለው የኔዋ አንቺም እኮ ለልጆቻችን የምታወረው ትልቅ ታሪክ አለሽ ሀገራቸውን እና ህዝባቸውን እንዲወዱ ህይወታቸውንም ሳይቀር ሳይሰስቱ እንዲሰጡ የሚያደርግ እውነታ አለሽ።

ታዲያ ውዴ ይህ ማለት በእንቺ እና በልጆቼ ብሎም በሀገሬ ልብ ውስጥ ኖርኩኝ ማለትም አይደል።

የኔዋ እማዬን አደራ ጠንቀይ እና ሀኪም ስለ እራሱ አያውቅም አይደል የሚባለው ፈጣሪ ብሎ የቀዘቀዘው ቤታችን ዳግም ይሞቅ ይሆናል ::

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)



## ያነቡ እንባዎች አስራ አምስት

የኔ ውዱ ጌታ ....

የአልበስጥሮስን ብልቃጥ ፡ ከፊትህ መስበሬ ፤

በናርዶሱ ሽቶ ፡ እግርህን ማበሴ ፤

ለምን ይመስልሃል....

አንተ ስር ወድቄ ፡ እንባዬን ማፍሰሴ ፤

ለምን ተብለህ ፡ አንተ አትጠየቅ ፤

በእኛ መረዳት ፡ ከቶ አትገመት ።

ግና....

ከአንተ ስር ሆኜ ፡ በብዙ ማንባቴ ፤

የእንባ ሽንትር ፡ በእግርህ ላይ ማፍሰሴ ፤



Scanned with CamScanner

እንዲህ ነው ነገሩ ፤

ወዲህ ነው ውሉ ፤

በአንድ ሸራ ላይ ...

ቀለሙን ቀይጦ ፡ ነክሮ የሳላቸው ፤

እግርህ እና ህይወቴ ፤

አንድ ነው መልካቸው ፤

መንታ ነው ገፃቸው ።

ለምን ይመስልሃል ፡ አንተ አትባል ፤

ከአንተ ሚደብቅ ፡ ስውር ነገር የታል ?

እነዚህ ያንተ እግሮች ፤

ከፍ ዝቅ እያሉ ፡ በህይወት መንገዶች ፤

ዕሩቅ ሄደዋል ፡ ሰርክ ተጉዘዋል ።





የኔ ውዱ ጌታ ፡ እቀበት ወተሃል ፤

እንዝፍ እያልክ ፡ ቁልቁለት ወርደሃል ፤

እነዚህ እግሮች ፡ ያልሄዱበት የለ ፤

አዳምን ለመማር ፡ ወጡ ወረዱ ፤

አንዷት አሮጊት...

የጎበጠች ድሃ ፡ መርገሟ በርትቶ ፤

ያዘነ አባት !

የልጁ ህሜም ፀንቶ ፤

የልብሱን ጫፍ ፡ ጨርቁን የነካች ፤

ደሟ እንደሚቆም ፡ በእምነት የተሞላች ፤

ህዝቡ በረሃብ ፡ ሲቆላ ሲታመስ ፤

በሁለት አሳ እና በአምስት እንጀራ ፤



Scanned with CamScanner

ረሃባቸውን ስትመልስ ፡

የዳዊት ልጅ ሆይ !

ማረኝ እያለ ፡ ጎበዙ ሲጣራ ፤

እምነቱ አድኖት ፡ አይኑን ስታበራ ፤

ያቺን አመንዝራ ፡ በድንጋይ ሊወግሯት ፤

በክስ ፍርዳቸው ፡ ከፊትህ ሲጥሏት ፤

የአብን ቃል ይዘህ ፡ ሁሉ ጋር ደርሰሃል ፡

በእነዚህ እግሮችህ ፡ ሰላምን ሰተሃል ።

እነዚህ እግሮች ፡ ያልሄዱበት የሉ ፤

አዳምን ለመማር ፡ ወጡ ወረዱ።

እንደነዚህ እግሮች ፡ እኔም ባዝኛለው

ለፅድቅ ሲሆኑ ፡ ለአመፅ ሆኛለው





የከፉትን ጥጋት ፡ በህይወቴ አይቻለው ፤

የሀጥያትን ድሪቶ ፡ ተከናንብያለው ።

እናም የኔ ጌታ...

የህይወትን መስመር እየተከተሉ ፤

እኔን ለማዳን ፤

እነዚህ እግሮች ፡ ዋጋን ከፈሉ ።

እኔን ለማንፃት ፡ እነሱ ቆሸሹ ።

ታዲያ ዛሬ ፡ አንተ ፊት ወድቄ ፤

እግርህን ማበሴ ፡ ባነባው እንባዬ ፤

ይህ ነው ነገሩ ፡ ወዲህ ነው ውሉ ፤

እኔን ለማዳን ፡ በብዙ ስለዛሉ።



Scanned with CamScanner

## ያነቡ እንባዎች አስራ ስድስት

ለአንዲት እናት የምጥ ጊዜዋ ለእሷ እጅግ ከባድ ነው። በህይወት ዘመኗ ተጋፍጣ የማታውቀውን ህመም የጣር ጩኸት ለቅሶ ትጋፈጣለች። ምክንያቱም በአለማችን ላይ ካሉት ከባድ ህመሞች መካከል የምጥ ህመም እጅጉን የከፋ እና የአንበሳውን ድርሻ ስለሚይዝ እና በአንድ ጊዜ ብዙ አጥንቶች ስለሚሰበሩ እንዲሁም የማህፀን በሮች ስለሚከፈቱ ያኔ ለእሷ ጭንቅ ነው በላብ ትሰምጣለች በህመም ትዋጣለች ግና ልጇን ወልዳ ወይም ከእነልጇ ሞታ ያኔ እፎይ ትላለች።

ግን ምን ያደርጋል ሀኪሙ ጎዳት እንጂ አውቀቱም መቀሱም ነበረው ውርጃ አግባብ ባይሆንም እናቱን ለማዳን አግባብነት ነበረው  ግን አልተቻለም ማድረግ





አቃተው :: ሰው ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ማህፀኗን ሲጠብቃት የከረመው ይሄው በምጧም ሰዐት ጭንቀቷን አባበሰው።

እናም ይች እናት ፡ ማንን ትመስላለች ፤

የሀገሬን ገፅታ ፡ ከሩቅ ታወራለች።



Scanned with CamScanner

## ያነቡ እንባዎች አስራ ሰባት

ወንድም ለወንድሙ ፡ ጥርሱን ነከሰ ፤

ባል በፍቅሩ ላይ ፡ ሰይፉን መዘዘ ፤

ሚስኪኖቹ ራቁ ፡ ደጋጎች ደየሙ ፤

እታች መሬት ወርደው ፡ አፈር ቃሙ ።

አበቦች ረገፉ ፡ ድንጋዮች ነገሱ፤

በሁሉም ፅንፍ ፡ አላዋቂዎች በዙ፤

ስመናል እያሉ ፡ ንፍጥ ለቀለቁ ።

ሁሉ ስርዐት አጣ ፡ ወዘናው ጠፋበት ፤

አይኑን ማስለቀስ ልማዱ ሆነበት ።





## ያነቡ እንባዎች አስራ ስምንት

አንዳንድ ቀናቶች ተመሳሳይ ስያሜ ይይዙና ግና ከአቻዎቻቸው ደምቀው ወይም ደብዝዘው ይታያሉ። ለዛም ይምስለኛል ያለፈችው ሀሙስ እኔ ጋር የከፋችው ፤ በህይወት ዘመኔ ተሰምቶኝ የማያውቅ ስሜት እንዲሰማኝ አደረገችኝ ። አንዳንዴ ሳስበው እኔ ምን አደረኩኝ እልና በእሱ ሃሳብ እሩቅ እንዳልጓዝ ህሊናዬ ጠፍንጎ ይይዘኛል መልሶ ወደ ኋላ ይጎትተኛል ለምን ለምን እያልኩ እራሴን እንዳስጨንቅ ድምፅ አልባ ጩኸት በውስጤ እንዳስተጋባ ያደርገኛል ። ከህሊናዬ መሸሽ መራቅ መደበቅ አቃተኝ ነገሩን ለማስተካከል አስብና መውጣት በማልችለው አዘቅጥ ውስጥ የምገባ ይመስለኝና እተወዋለው።



Scanned with CamScanner

ያኔ እራሴ ክፉኛ ይታመማል በሁለት እጆቼ እራሴን እንደያዝኩ በሰመመን በምልሰት እከንፋለው ፤ ሽምጥ እጋልባለው ማረፊያዬ መሸሸግያዬ ያቺ ከቀኖቼ ሁላ የተረገመች ሀሙስ ትሆናለች።

በዚያች ሀሙስ ድንገት ስልኬ ጠራ ትርሲት ናት ፤ አየውትና ወደ ኪሴ መለስኩት ዳግም ደወለች ፡ ማንሳት አልፈልኩም ከፊት ለፊቴ ከተሰየመው ጠረጴዛ ላይ ስልኬን ወረወርኩት ። ለምን እንደደወለች ለመገመት ብዙም አልተቸገርኩም የትርሲት የዘወትር ጥያቄዋ አንድ ነው እወድሃለው....እወድሃለው....እወድሃለው ብቻ ነው መወደድ እኮ መታደል ነው መውደድ መቻል ደግሞ አንድ የተፈጥሮ ህግ እና ጤናማ የመሆናችን ምልክት ነው። እሱስ መቼ ጠፋኝ ፍቅር እኮ ውበት የሚኖረው ዜማውም ቅኝቱ የሚጠብቀው ከሁለቱም ወገን ብቻ ሲሆን መሆኑን እኮ ትርሲት መረዳት አለባት ብነግራት ብሰራት አይሆኔ ብሆንላት ልትረዳ አልቻለችም ።





እሺ እኔ ምን ላድርግ? እንዴት ልውደዳት? እንዴት ላፍቅራት? እንደ እሷ ምኞት እንዴት ልስከር ከልጅነታችን ጀምሮ ጭቃ እያቦካን ባቦካነው ጭቃ ጥቢኛ እየጋገርን ከሰፈር ልጆች ጋር ጂሪካን ቆርጠን እንደ ከበሮ እየደለቅን በዛ በዝናቡ ዶፍ ባለቀሰው ከእሸሁ ላይ አበባ ቆርጨ ለፀጉሯ አስሬላት አዎን ተጋብተን ነበር ። ትርሲት የልጅነት የህፃንነት ፍቅሬ ነበረች ሌሎች ወንዶች አፍጥጠው ሲመለከቷት በቅናት ውስጤ ይንጨረጨርና በሳማ እገርፋቸው የነበረው ስሜት አሁን እኔ ጋር የለም ልጅነቴ ሲጠፋ ይዞት የሄደ ይመስለኛል ። ትርሲት ጋር ግን እንዴት ቀረ ? እሷ ጋር ብቻ ዕድሜዋን ተከትሎ እንዴት አደገ በልጅነት የመሰረትነው የዕቃቃ ቤታችን አድጎ እሱም በተራው የኔ እና የትርሲት ልጆች የሚያድጉበት ቤት ለመሆን እሷ ጋር ብቻ እንዴት አሰበ ? ይህ የዘወትር የሁል ጊዜ እራሴን የምጠይቅው ጥያቄ ነው ።



Scanned with CamScanner

ማንም ሰው እህቱን ከሚወደው በላይ እወዳታለው አንዳንዴ አንድ ማህፀን ተጋርተን የወጣን ይመስለኛል ። ሴቷ አያቴ አንድ ቀን ደጅ ላይ ተቀምጣ ፀሃይ እየሞቀች በደከመው ድምፂ ጠራችኝ

«ልጄ ...ልጄ...»

አቤት አያቴ ጠራሽኝ አልኳት ከላይ የለበሰችውን ነጠላ እያስተካከልኩላት።

«እስኪ ተመልከታት የዛሬዋን ሃሙስ ደስ አትልም» አለችኝ ፈገግ እያለች እንውለቅ አንውለቅ የሚሉትን ሁለቱን ጥርሶቿን እያሳየችኝ ።

መቼስ አያቴ ፀሃይዋ ስላላቃጠለችሽ ይሆናል እንጂ ከወትሮው የተለየ ደስ የሚል ምን መልክ አላት ብለሽ ነው አልኳት ? ከአጠገቧ ቁጢጥ ለማለት እየሞከርኩ ።





«እሱም አንዱ ነው እስኪ ሰውን ተመልከት ሁሉም የራሱን ሃሳብ አላማ አንግቦ ወዲህ ወዲያ ይላል የዕለት ቁርሱን የዕለት ጉርሱን ሊሞላ ሁሉም በየ አቅጣጫው ይማስናል ። ያቺን እናት ተመልከታት ልጇን በአንቀልባዋ እንደያዘች በአንድ እጇ ዘንቢል ይዛ ጉልት ትወርዳለች።

ለምን ለልጆችዋ ስትል ...ታዲያ ፈጣሪ ጤና ሰጥቶህ ወዲህ ወዲያ እያለ የሚማስነውን ሰው ከመመልከት በላይ ደስታን የሚፈጥርልህ ምን አለ ብለህ ነው ልጄ ። ሁሉም ሸጋ እና ሰናይ ቀን ይሁንልኝ ብሎ የወጣ አይመስልህም» አለችኝ አይን ኤኔን እያየች። ደከም ያሉት የአያቴ አይኖች ከእኔ ምላሽ እንደፈለጉ ያሳብቅባቸዋል ።

ልክ ነሽ አያቴ ሀሙስም የቀን ቅዱስ አይደለች ሀሙስን መስላለች አልኳት ቀጥሎ የምትለኝን ለመስማት እየተዘጋጀው።

«በሕይወት ዘመንህ ሁል ጊዜ በልብህ ፅላት ላይ እንዳትረሳ አድምቀህ የምትፅፋቸውን እና



Scanned with CamScanner

የምትከተላቸውን ሁለት ነገሮች ልንገርህ» አለችኝና በቀኝ እጇ ፀጉሬን ስትዳብስ ልጅ የሆንኩ መሰለኝ፡፡

በጣቶቻዋ መሃል የተደበቀው ወርቅ መሰይ ቀለበት ጣቶቸዋን ተከትሎ በፀጉሬ ውስጥ ተደበቀ፡፡

« በመጀመሪያ ልጄ እስኪ የፀሃይን ብርሃን ተመልከት እስኪ ቀና ብለህ ተመልከታት እስኪ ቀና ብለህ እያት አየሃት አንድ ሆና ለአለም ህዝብ በሙሉ ሆናለች አንዳንዱ ልክ እንደ እኔ በዱካው ላይ ቁጭ ብሎ ይሞቃታል እናቶች ህፃናቶቻቸውን በቅባት እሽት አድርገው ያሻሉ፡፡ ገሚሱም ያጠበው ልብስ እንዲደርቅለት ያሰጣል ብቻ ልጄ ሁሉም እንዳሰበው እና እንደ ፍላጎቱ ይጠቀማታል ግን እስኪ ይህችን ጥያቄ መልስ ተምረናል ተመራምረናል ትሉም የለ ይህንን የፀሃይን ብርሃን ፈጣሪ ስብስብ አድርጎ አንድ ነገር ላይ ብቻ ቢያደርግ ምናልባት ደጅ ላይ ብቻ ተቀምጦ ለሚሞቀው ጀርባውን ለሚያስመታው ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ በእነዝያ እናቶች ህፃናት ላይ ወይም





የከበቡሽ ብቅል ላይ ብቻ አንዱ ላይ ቢደረግ ምን የሚፈጠር ይመስልሃል» አለችኝ ያልጠበኩት ያላሰብኩት ጥያቄ ሆነብኝና በአያቴ ተገረምኩ፡፡

እንዴ አያቴ ብርሃን እኮ ትልቅ አቅም እኮ አለው ብርሃን ውስጥ ደግሞ ሙቀት አለ ሙቀት ደግሞ ብረትን ሁላ እስከ ማቅለጥ ድረስ ትልቅ አቅም አለው፡፡ የፀሃይ ብርሃን ደግሞ አስቢው አያቴ የአለም ህዝብ ሁሉ ላይ አርፋ እንደዚህ ከሆነች በአንድ ሰው ላይ ብቻ ብትሆን አስበሽዋል ልክ እንደ ሻማ ይቀልጣል አልኳት፡፡ አያቴ ምን ልትነግረኝ እንደፈለገች ከቀድመው ይልቅ ለማወቅ እየጓጓው ፡፡

«ጎበዝ የኔ ልጅ ለአያትህ እኮ ነው የወጣከው አባትህ ትንሽ ፈዘዝ አለ እንጂ ፡ እንግዲህ ልክ ብለሃል እኔም ልነግርህ ያሰብኩት ይህ ነው የምትሰራቸው ነገሮች ስመለከት ጥሩ ናቸው፡፡

የህክምና ትምህርቱንም እየተማርክ ነው በዚህ ደግሞ ግጥም ትፅፋለህ ክበባት ላይ ትሳተፋለህ ባልወድልህም ዳንኪራ ላይ ሽር ጉድ ትላለህ ፡፡ ቆንጆ እና መልካም ናቸው ግን አንድ ስጋት አለኝ ልጄ እንደዚህች የፀሃይ ብርሃን ለሁሉም ስትሆን አንዱን ነገር ማቅለጥ እንዳያቅትህ ፈራለው ቅድም አንተም ብለህ የለ ያንን ሁሉ የፀሃይን ብርሃን ሰብስበን ለአንድ ነገር ካደረግን ልናቀልጠው እና ልናጠፋው እንችላለን አላልክም በል እንግዲህ ይህችን የህይወትህ መመሪያ አድርጋት ፡፡ ሁሉ ነገርህን ጉልበትህን ጊዜህን የያዝከውን ነገር ላይ እስክታቀልጥ ሰብሰብ አድርገህ አንድ ነገር ላይ አድርግ በመጀመሪያ የምልህ ይህ ነው ፡፡





ሁለተኛ ደግሞ ህርም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ?» አለችኝ አላውቅም አያቴ አሁንም መልስ ከእሷ እየጠበኩኝ ህርም ማለት ልጄ ረሃብም ይምጣ ችነፈር ድርቅ ይከበበኝ በቤቴ ይሙላ በረሃብ አለንጋ ልገረፍ ልቆላ ልቃጠል እንጂ መቼም ቢሆን የሰውን ስጋ አልበላም ማለት ነው ፡፡

አንዳንዴ በህይወትህ አንዳንድ ነገሮች ህርም ሊሆኑብህ ይገባቸዋል እንደዚህ ቢሆን ይህን ነገር አልፈፅምም ብለህ ለእኔ ህርም ናቸው ብለህ የምታስባቸው ነገሮች መኖር አለባቸው፡፡ እነዚህን ሁለቱን ነገሮች አትርሳቸው ዛሬ በዚህች ውብ ሃሙስ የምልህ ነገር ቢኖር ይህ ነው በል ተነስ ና አንሳኝ አሁን እየበረታች ነው ቅድም እንዳልካት ሻማ ሳንቀልጥ እንግባ» አለችኝና ተያይዘን ገባን፡፡ ከአመታት በፊት አያቴ በዚያች ሃሙስ ካስተማረችኝ ትምህርቶች መካከል አንዷን የሳትኩ መሰለኝ ትርሲት ለእኔ ህርም ናት ብዬ ሚዬ ተገዝቻለው፡፡

በሃገሪቱ ሴት እንኳን ባጣ እንደ እህቴ የምመለከታትን ትርሲት ከእህትነት ውጭ እንደማላስባት ልበናዬ ያውቃል፡ ፡ ለዛም ነው ስትደውልልኝ ያላነሳውላት ለዛም ነው የሸሸዋት እህትነቷን አስበልጬ ዝም ያልኳት ለሶስተኛ ጊዜ ስልኬ ጠራ የዘሬው ይለያል ትርሲት ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ ደውላ ካላነሳው አኩርፋ ትዘጋለች ለአራተኛ ጊዜ ጮኸ ያኔ አነሳውት ሄለው ትርሱ....

«አሁንም እንደለመደቸው ትጨቀጭቀኛለች ብለህ ነው የማታነሳውን?» እንደ ተናደደች ድምፇ ያስታውቃል ። አላየውትም ልላት አሰብኩና መዋሸት አቃተኝ ምላሽ ሳልሰጥ ዝም አልኩ ። «አሁን ቶሎ ብለህ ቤት ና አሞኛል አከራዮቼ የሉም ። » ማለት ምን ሆንሽ ቆይ እሽ መጣው ያኔ አንደበቴ ተከፈተ የወንድምነት ስሜት ብልጭ ብሎ ሲወጣ ታወቀኝ ። መጣው.... መጣው...ስልኩን ዘጋውትና እየተክለፈለፍኩኝ እራሴን ከተከራየቸው ቤት ደጃፍ ላይ አገኘውት ።





ገርበብ ያለውን በር በርግጄ ገባው የጠበቀኝ ያላሰብኩት ነገር ነበር ። ቤቱ በሻማ አሸብርቋል ድንግዝግዝ ያለው ብርሃን መሬት ላይ ከተቀመጡ ሻማዎች እና ከቀለ ጥቅልል ወረቀቶች ይታያል ፤ በአይነት በአይነት ያሸበረቁ የወረቀት ቁራጮች የአበባውን ፈንታ ሸፍነው ቤቱን አሳምረውታል በትንሹ የቴልቭዥን ማስቀመጫ የቴልቭዥኑን ቦታ ተክቶ ከጠቀመጠው ጂፓስ ለስለስ ያለ ሙዚቃ ይሰማል ።

በወፍ በረራ ቤቱን አየውት ለምን እንደሆነ ምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም። አይኔን ወደ ትርሱ መለስኩ ጥቁር ቀሚስ ለብሳለች የለበሰችውን ቀሚስ በጉልበት በልጠው የወጡ ጡቶቸዋ ለአይን ደስታን ይጭራሉ በጡቶቸዋ መካከል ያረፈው መስቀል ቦታው የተመቸው ይመስላል ከፀጉር ማሳዥያዋ ያመለጡ የዝንፍል ፀጉሯ ዘለላዎች አንዳንዶቹ የመስቀሉን ቦታ ይጋፋሉ። ፈገግታን ተችራ በአይኖቿ ገረመመችኝ በጠረጴዛው ላይ ወይኑ ተቀምጧል ። ጥቁር የወይን ደም በሁለት ብርጭቆ



Scanned with CamScanner

ሞልቷል ምን እንዳሰበች ለምን እንዳደረገች አሁንም ሊገባኝ አልቻለም ። በሁለት እጆቻዋ ቀሚሷን እንደ ያዘች ቀስ እያለች ወደ እኔ ተጠጋች ፤« እንዳስደነገጥኩህ አውቃለው ዝም ብዬ ና ብልህ እንደማትመጣ እና ሰበብ ፈጥረህ እንደምትቀር ስለማውቅ ለዛ ነው የዋሸውክ እባክህ ይቅር በለኝ አለችኝ በእጆችዋ ፂሜን እያሻሸች »።

ትርሲት ግን ግራ እያጋባሽኝ ነው ውሸቱስ ይሁን ግን ምንን በማስመልከት ነው ቤቱን ድግስ በድግስ ያደረግሽው? ወንበር ስቤ እየተቀመጥኩኝ።

«ዛሬ ቀኑ ምንድነው?» ከጠገቤ እየተቀመጠች ። ቀን መያዝ ላይ ብዙም እንዳልሆንኩ እያወቅሽ ከሷ መልሱን እየጠበኩኝ ። ሀሙስ ህዳር አስራ ሁለት እና ለምን እንዳደረገች በትንሹ እንደተረዳዋት ፊቴ ያሳብቃል ። «እና ህዳር አስራ ሁለት ምን እንደሆነ አታውቅም ?» ከቀድመው ይልቅ ቆጣ ቆጣ እያለች ። ህዳር አስራ ሁለት ሲመጣማ ከዚህ ቀደም በኢትዮጲያ የህዳር በሽታ





እየተባለ የሚታወቀው እና የአንደኛውን የአለም ጦርነትን ፍፃሜ ተከትሎ አለምን ያዳረሰው በታሪክ እስፓኒሽ ፍሉ በመባል የሚታወቀው የኢንፉልዌንዛ ወረረሽኝን የሀገሬው ህዝብ በአንድ ላይ በመሆን ሀገሪቷን በጪስ በማጠን በሽታውን ድራሹን እንዳጠፋ ታሪክ ያትታል ። እስካሁንም ይሄው የሚካኤል ዕለት ቆሻሻ ሰብስቦ ሲዘክር ይታያል ይሄ ነው እንግዲህ ትርሱ ።

«እያወክ ግን ለምንድነው የምትጫወትብኝ ዛሬ ልደትህ እንደሆነ አታውቅም?» በአይኗ ላይ እንባ እየቀረረ

እሺ ትርሱ ተረጋጊ ሲጀመር እኔ ከመቼ ጀምሮ ነው ልዴቴን ማክበር የጀመርኩት? ለሰርግ ለልደት ግርግር ለሚበዛባቸው ነገሮች ብዙም በታ እንደሌለኝ እያወቅሽ ፡ ስለ እውነት ደግሞ ዛሬ ህዳር አስራ ሁለት መሆኑን ረስቼዋለው ። አንቺ ካላስታወሽ ደግሞ ማን ያሰታውሰኛል ላፅናናት እየሞከርኩኝ አይኖቼ ድንገት

በፍርጁ ላይ ወደተቀመጡት ሁለቱ ሻማዎች ላይ አረፉ ። አ! ሻማም አዘጋጅተሽልኛል በስተ እርጅና ፈንዲሻ እያፈስኩ ሻማ እያበራው ልደቴን ላከብር ነው በቃ ተነሺ ሻማውን እንለኩስ ሙዚቃውን ከፍ እናድርገው አልኩና ተያይዘን ተነሳን የምርም ደስ ብሎኝ ነበር ። የውልደቴን ቀን ሁሉም ረስተውታል ትርሱ ግን እንደዛ እየገፋዋት ቀልቤን ገዛችው ልቤን ገዘተችው ሌላ ሰው ሆንኩኝ ። በአፈር የሰራነውን ጥቢኛ እንደቆረስን ዛሬም ከእሷ ጋር ሆነን ዳበውን ቆረስኩት በቆርኪ ጠላ ነው እያልን እየቀዳን እንደ ጠጣነው ወይኑን ደግመን ደጋግመን ጨለጥነው። ለሁለት ዘለልን በራሳችን ዐለም እሩቅ ተሰደድን በሞቅታ ወደቅን። በሳሎኑ ጥጋት ወደ ተነጠፈው ፍራሽ ወሰደችኝ በወይን በቀሉ ከንፈሮችዋ ከንፈሬን ጎረሰችው በስሜት ሹረት ቃተትን ሰከርን በስሜት ሁለታችንም ግለን ድንገት ሳናስበው በብርሃን ፍጥነት ፍራሹ ላይ ወደቅን ። በሁለት እጆችዋ ዳሌዬን ጨመቅ አደረገች ከንፈሬ በእሷ ከንፈር





እንደተጎረሰ የፍቅርን ዜማ ማዜም ጀመርን ፡ማቃሰት የጋለ ስሜት የተንቻፈቻፈ ላብ ከፊል ጨኸት

የደም ጠብታ በትራሴ ላይ ሲፈራረቅ ታወቀኝ ። ድንግል እንደሆነች አውቅ ነበር አሁን ደግሞ አረጋገጥኩኝ ከአይኖቿ ትኩስ የእንባ ሸንትር እንደ ወንዝ ይፈሳል ። ማለቂያ የሌለው ያነባ እንባ ይወርዳል በእሷ እንባ ውስጥ ነገን አየውት በሷ እንባ ውስጥ ከዚህ ድባብ ስንወጣ ያለውን ስሜት አሰብኩት ። ፈራው በፍርሃት ተዋጥኩኝ ያኔ ምንም ሳልናገር እየተንገዳገድኩኝ ተነሳው በየ በታው የጣልኩትን ልብሴን ለብሼ በሌለብኝ አመል መንደርተኛው ጣቱን እየቀሰረብኝ ቤቴ ገባው።

ይሄው ከዚያች ቀን ጀምሮ ከቤቴ አልወጣው ያች ሀሙስ ከፋችብኝ ማን ነበር ሃሙስ የቀን ቅዱስ ያለው ድንቄም የቀን ቅዱስ እንደ እህቴ የማያት ትርሲት ከደስታ እና ከጥልቅ ስሜት ባሻገር ነገን የሚያወሩ የትርሲት ያነቡ እንባዎች እንደ መስታወት ፊቴ እየተደቀኑ አልጠፋ አሉኝ

መልካም ጓደኝነትን አብሮነትን ተግባቦትን ሸጋ ስብዕናን አንድነትን ለመገንባት አመታት እንደሚፈጅ ሁሉ ይህንኑ ለመናድ ደቂቃዎች በቂ መሆነቸው ገባኝ።






ልዩ ምስጋና

- ለ አቶ አርጋው አየለ
- South Star international Hotel Hawassa

  Tel: 0462201616

  Fax : 0462200311

  Mob : 0932670951

  Email :

  info@southstarinternationalhotel.com
- ፋሚሊ ህትመት እና ማስታወቂያ ስራ ድርጅት

  0972721121- 0934977872




ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)

Scanned with CamScanner